# የፈውስ ቀውስ

ከሁለት ዓመታት በፊት ቤኒ ሂን ሲያካሂድ በነበረው የ'ፈውስ' እና "በመንፈስ መሰየፍ" (slaying in the Spirit) 'አገልግሎት' ወቅት አንዲት ወፍራም ሴት በአንዲት አሮጊት ላይ በመንገደቧ የአሮጊቷም የዳሌ አጥንት በመሰበሩ የ5 ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፍል ተጠይቆ ነበር።

በ1988 ዓ.ም. ደግሞ በመቱ ከተማ ታላቅ የፈውስ ጉባዔ እንደሚደረግ የሚናገሩ ማስታወቂያዎች እየተለጠፉ ብዙ የበሽታ ዓይነቶች እየተጠሩ ድውያን ወደ ጉባዔው ቦታ ታደሙ። ጉባዔው የተካሄደው ለሦስት ቀናት ሲሆን ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ውጤቱን ብቻ ልናገር፤ በነዚህ ሦስት ቀናት ውስጥ በዓይን ከሚታይና በአካል ከሚታወቅ በሽታ የተፈወሰ አንድም ሰው አልነበረም። በሁለተኛው ቀን ደግሞ የሚዘገንን ታሪክ ተፈጸመ። ፈውስ ፍለጋ ወደ መድረክ የሄደች የልብ ድካም የነበረባት ሴት እመድረክ ላይ ወድቃ ቆይታ ሞታ በዕለቱ ማብቂያ ላይ ከአዳራሹ ሬሳዋ ወጣ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያውም በምዕመናን መካከል ለሚፈጸሙ ይህን መሳይ አሳፋሪ ነገሮች ቃሉም መሪዎችም የዝናን ጅሮና የዓሣ አንደበት ይስጠኝ ሊሉ አይገባም።

በዚህ ዘመን ሕመምን፥ ፈውስንና ጤንነትንም በተመለከተ የታቀወሰ አመለካከት አለ። ይህ አመለካከት በጥቅሉ "አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የክርስቶስ አካል ሆኗልና ማናቸውም ዓይነት ስጋዊ መከራና በሽታ ሊነካው አይችልም፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለክርስቲያን የተሟላ ጤንነትና ቅጽበታዊ ፈውስ ነው። ጤንነት የጤናማ ክርስትና ሕመም ደግሞ የበሽተኛ ክርስትና ምልክቶች ናቸው" የሚል ነው።

እንዲህ ያለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ራሳቸው አይታመሙም ማለት አይደለም። እየታመሙ ብዙ ያሳለፉ አሉ። ክርስቲያን መታመም የለበትም የሚሉ ሰዎችን ሲታመሙ ሁለት መጥፎ ነገሮች ይጋፈጧቸዋል። የመጀመሪያው ያንን ሕመም ስለማይጠብቁት እንዴት አድርገው እንደሚያስተናግዱት ግር ይላቸዋል። ሁለተኛውና ከዚያኛውም የባሰው ደግሞ በሽታውን አይቀበሉትም እያሳመማቸው እንደሌለ ይቆጥሩታል፤ ይክዱታል። እያደር የሚጠና መጥፎ በሽታ ምልክት እንኳ ቢሆን 'ውሸት ነው' ይሉታል እንጂ መከላከያ ሊወስዱ አይቃጣቸውም። መድኃኒት መውሰድ ደግሞ መፍራት ሲሆን ፍርሃት ደግሞ በተራው በሽታውን የማሳደጊያ ቀለብ ነው ብለው ይገምታሉ። በሽታው ስለተካደ የለም ማለት አይደለም። 'ክርስቲያን ሳይንስ' የሚባለውና ሌሎችም መሰል ዲበ አካላዊ (metaphysical) የስህተት

ትምህርቶች ሕመምን እውን እንዳልሆነ እንደ አንድ ዓይነት ቅዠት ይቆጥሩታል።

ሰው መጀመሪያ ለምንም ዓይነት ጉስቁልና አልነበረም የተፈጠረው። ሊሞትም አልነበረም። መርገም የመጣው ከሰው ኃጢአትና ውድቀት በኋላ ነው። ሕመምና ስቃይም የዚህ ፍርድ ቅርንጫፎች መሆናቸው ግልጽ ነው። እነዚህ ነገሮች ማንንም አይመርጡም፥ ማንንም አይለዩም። አንዳንድ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ቢከሰቱ እነዚህ ነገሮች ሆን ብለው ክርስቲያን ያልሆኑትን ብቻ እየመረጡ ያጠቃሉ ማለት አይደለም። እዚህ ላይ መካድ የሌለበትም ሐቅ አለ፤ ያም እግዚአብሔር ጠባቂ አምላክ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር መቅሰፍትን በግብጽ ላይ ሲልክ ጌሴምንና በውስጧ የነበሩትን እስራኤል ሁሉ ጠብቆ ነበር። ግብፅን ለቀው ከመውጣታቸው በፊትም አጥፊው መልአክ በመቃኑና በጉበኖቹ ደሙ ያለበትን በር እያለፈ ይሄድና ባልተቀባበት ቤት እየገባ በኩሩን ይገድል ነበር። ጌታ ሕዝቡን እንደሚጠብቅም ብዙ ተስፋ ሰጥቷል።

የእግዚአብሔርን ጠባቂነት ስናስብ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወታችን የወደደውን ቢያደርግ ማንም የማይጠይቀውና የማይቆጣው አምላክ የመሆኑንም እውነት ማለፍ የለብንም። ሲያጠፉ ይቀጣል፥ መልካም መስሎ ከታየው ደግሞ ባያጠፉም ለመጠበቅና ለማስተማር ወይም እኛ ለማናውቀው ወይም ልናውቀው ለማንችለው ምክንያት እኛ የማንወደውን ቅጣት የሚመስልን ነገር ወደ ሕይወታችን ሊያመጣ ይችላል። በርግጥ እንደ ጥፋታችን የማይቀጣን አምላክ ቢሆንም አጥፍተን ከሆንና ካወቅነው ልንታረም ካልሆነም በአባታዊ ፍቅሩ ታምነን ልንታገሰው ይገባናል። ስለ ቅጣት ስናስብ ከግብፅ ከወጡት እስራኤል የሚበዙቱ በምድረ በዳ ወድቀው መቅረታቸው ምሳሌ ሊሆንልን ይችላል። ሳያጠፉ ፍዳን ለተቀበሉት ኢዮብን፥ ለታመሙትም ጳውሎስን ጢሞቴዎስንና ሌሎችንም እንደ ምሳሌ ልንወስድ እንችላለን።

የዚህ 'ክርስቲያን መታመም የለበትም' የሚለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንጥብ የሚነሳው ከኢሳ.53:4-5 እና ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሰባቸው ሁለት ቦታዎች ማለትም ከማቴ.8:16-17 እና 1ጴጥ.2:22-25 ነው። ዋናው የትምህርቱ አሳብም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል በሽታችንንም ሁሉ ነው የተሸከመልን እና ከመስቀሉ ወዲህ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በበሽታ መነካት የለባቸውም የሚል ነው። እንደነዚህ ሰዎች ትምህርት ስጋዊ ሕመም የመንፈሳዊ ችግር (የውስጣዊ/መንፈሳዊ በሽታ) ውጪያዊና አካላዊ ምልክት ሲሆን ከመንፈሳዊ ሕይወት ያለመስተካከል የሚመጣ ነው። በተጨማሪም የሰው አሉታዊ ንግግር (Negative Confession) በሽታን

ያመጣል። በአሳብም ይሁን በቃል በሽታ በአካላችን እንዳለ ስናስብና ስንናገር ሰይጣን ዕድል ያገኝና ይወርረናል በሽታም ይይዘናል ይላሉ።

> የእምነት አስተማሪዎች ደጋግመው ይህን መሳይ ማስጠንቀቂያ ለጉባዔያቸው ይናገራሉ። በጣም አክራሪ በሆኑት (የዚህ) እምነት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ አንድ ክርስቲያን የጸሎት ጥያቄ ለማቅረብ እንኳን በሽታን መጥራት የለበትም። እንዲህ ያደረጉ ከኖሩ ይገሰጹና 'ቃሉን እንዲናገሩ" (የጌታን ቃል ማለት ነው) እና ስለተፈወሱ እንዲያመሰግኑ ይነገራቸዋ።[33]

ከዚህ መጠቅ ያለውን የሚያስተምሩት ደግሞ አንድ ክርስቲያን ከ70-120 ዓመት ሳይሞላው መሞት እንደሌለበት ያስተምራሉ። ከነዚህ የባሱት ሌሎች ደግሞ (ለምሳሌ 'የተገለጡት የእግዚአብሔር ልጆች' የሚባለው ማኅበር) አንድ ክርስቲያን እንደነ ሄኖክና ኤልያስ መነጠቅ አለበት እንጂ ጭራሽ መሞትም እንደሌለበት ይናገራሉ።

ከላይ ባየናቸው ሦስት ምዕራፎች (ኢሳ.53፥ ማቴ.8 እና 1ጴጥ.2) ፈውስ የሚለው ቃል ተጽፏል። መጀመሪያ የተጻፈው በኢሳይያስ ሆኖ ማቴዎስና ጴጥሮስ ያንን ነው የጠቀሱት። በኢሳይያስ የተጠቀሰው የቃሉ ትርጉም (በዕብራይስጥ 'ራፋ' የሚባለው) መፈወስ፥ መዳን፥ ደህና መሆን፥ ጤናማ መሆን እንደማለት ነው። ቃሉ በብሉይ ኪዳን ሰፋ ተደርጎ ተጠቅሷል። ሁሌም የስጋ ፈውስን ብቻ አይናገርም፤ ለምሳሌ፥

- መሻር፤ (ቁስል፥ ቤት ወዘተ.) ዘሌ.13:18-37፤ 14:48
- መጥፋት (የለምጽ)፤ ዘሌ.14:3
- መፈወስ (ውኃ፥ ሰው፥ ከተማ፥ ባህር ወዘተ.) 2ነገ.2:22፤ ኢሳ.53:5፤ ኤር.3:22፤ 17:14 ፤ 51:8-9 ፤ ሕዝ.47:8-9

ኢሳ.53ን በሙሉ ስናነብበው የመሲሑን ስቃይ እናያለን። የመሲሑ ስጋ መልበስ ዋና ዓላማ ደግሞ ከኢሳ.53 ብቻ ሳይሆን ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ኃጢአታችንን ተሸክሞ ሊሞትና በሞቱም እኛን ሊያድን ነው። ይህ ነው ደኅንነት። ጌታ መሸከም የነበረበት ዕዳ እኛ መሸከም የነበረብን ነበር። የሕማም ሰውና ደዌን የሚያውቀው ጌታ ይህን የሆነው ለኛ ሲል እኛ ማለፍ የነበረብንን ግን ልናልፈው ያልቻልነውን የደኅንነት ጎዳና ለመሄድ

ነበር። ኢሳ.53:2-4ን የወሰድን እንደሆነ ስለ ራሱ ስለ መሲሕ ስጋና ስለ ስጋዊ ፈውስም ይናገራል። ጌታ ፈዋሽ መሆኑ በወንጌላት በግልጽ የተጻፈ እውነት ነው። ነገር ግን መሲህ የቆሰለው ስለ መተላለፋችን የደቀደውም ስለ በደላችን ነው። ይህ ነው የመሲሑም ስጋ መልበስ ዋና ዓላማ እንጂ ጌታ ስጋን የነሳው በሽታችንን በመስቀል ላይ ለመሸከምና ከሕመም ነፃ ሊያደርገን አይደለም። ኢሳ.53:5 ስለ ነፍስ ደኅንነት እንጂ ስለ ስጋ ጤንነት አይደለም የሚናገረው። ይህን ካልን የጌታን ስቃይ ዓላማ ከትልቁ ወደ ትንሹ አውርደን ዓላማውን ማሳትና ማቅለላችንም ይሆናል።

በማቴ.8:16-17 የተጻፈውን አሳብ ስንወስድ ደግሞ ይህ ጥቅስ የተጠቀሰው ገና ጌታ ሳይገረፍ፥ መከራ ሳይቀበል፥ ሳይሰቀልና ሳይሞት ነው። አዳኙና ፈዋሹ የተነገረለትም መሲሕ እርሱ መሆኑን ለማሳየት ይህ ጥቅስ ተጠቀሰ እንጂ የሰዎቹን ደዌ ለመሸከም ጌታ ገና በመስቀል ላይ አልዋለም ነበር። በመስቀል ላይ ከመዋሉ በፊት ድውዮቹን ፈውሶ ነበር። ጌታ ሰዎችን ከደዌ ለማዳን የግድ በመስቀል ላይ መዋል አልነበረበትም ሳይውልም ፈውሶ ነበርና። ለነፍሳችን ደኅንነት ግን መሰቀል ነበረበት! የመስቀሉ ዓላማ እንግዲህ በግልጽ የነፍሳችን ደኅንነት እንጂ የስጋችን ፈውስ አይደለም።

የጴጥሮስንም አጠቃቀስ ስናይ ተመሳሳይ እውነትን ነው የሚናገረው። መናገርም ይገባዋል። የጥቅሶቹን ዙሪያ ስንመረምር ስለስጋችን ሳይሆን ስለ ነፍሳችን ሲናገር ነው የምናየው። ጌታ የተሸከመው የስጋችንን ሕመም ሳይሆን የነፍሳችን በሽታ የሆነውን ኃጢአታችንን ነው። ቁ:22-23 የመሲሕን ማንነት ይናገራል። ቁ:24 ጌታ ያደረገውን ነገር ከነዓላማው ይናገራል። ጌታ ያደረገው በስጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ መሸከም ነው። ሌላ ነገር ሳይሆን ኃጢአታችንን ነው የተሸከመው። ዓላማውም ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር ነው። ለሌላ ከዚህ ላነሰ ነገር አይደለም። የጌታን የመስቀል ሞት እኛን ከማዳኑ ባነሰ ነገር መለወጥ ትልቅና አደገኛ ስህተት ነው። "በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" ሲል ስጋዊ ፈውስን ያለመሆኑ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው። ቁ:25 ደግሞ ምን እንደነበርንና ምን እንደሆንን ይናገራል። በተለይ ወዴት እንደተመለስን ይናገራል። በርግጥ ጌታ የስጋችንም ጠባቂና እረኛ ቢሆንም ጴጥሮስ ግን "ወደ ነፍሳችሁ ጠባቂና እረኛ ተመልሳችኋል" ነው የሚለን። ጴጥሮስም የኢሳይያስን መጽሐፍ በመጥቀስ የሚነግረን ኢሳ.53 ደኅንነት ሲል ስጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ደኅንነት መሆኑን ነው።

ለመሆኑ ጌታ ይፈውሳል? ቃሉስ ይህን ይናገራል? ጌታ በእርግጥ ፈውሷል ወንጌላት ይህን ይመሰክሩልናል። ሐዋርያትም ፈውሰዋል የሐዋርያት ሥራ ይህን ይነግረናል። ወንጌል ሲሰበክ ከሚከሰቱት ምልክቶች መካከል

አንዱ የድውያን ፈውስ ነው። (ማር.16:15-20) መፈወስ ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ ነው። (1ቆሮ.12:9) በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞች ሲታመሙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን እንዲጠሩ እንዲጸለይላቸው እንዲያደርጉና እንደሚፈወሱም ተጽፏል። (ያዕ.5:14-15) እነዚህ ሁሉ የጌታ ቃል የሚናገራቸው የፈውስ ኀልውና እውነታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ የስጋ ፈውስ የወንጌሉ ትንሽ ቁራጭ እንጂ ወንጌሉ በሙሉ ማለት አይደለም። ክርስትናም የዚህ ወንጌል መንገድ ከሆነ ወንጌሉ የሚነገርበት ቦታም ይህ አዋጅ የሚታወጅበት ቦታ እንጂ የስጋ ፈውስና በረከት ብቻ የሚታጨዱበት ቦታ መሆን የለበትም። በዘመናችን ወንጌል በስጋ የሚታይ ምልክት ካልታከለበት ወንጌል የመሆኑ እውነት አጠራጣሪ እየሆነ መጥቷል። እግዚአብሔር የወደደውን የሚያደርግ ሉዓላዊ አምላክ እንጂ የወደድነውን ብቻ የሚያደርግ አገልጋይ ባለመሆኑ ፈቃዱን ሊፈጽም ቦታው አይነካበት። እርሱ እግዚአብሔር ነውና የወደደውን ቢያደርግ ያድርግ ባያደርግ ደግሞ እንዲያደርግ ማን ያስገድደዋል? እግዚአብሔር ቢፈልግ ሊሰጥ ወይም ሊነሳ፥ ሊጥል ወይም ሊያነሳ፥ የወደደውን ሊሾም ወይም ሊሽር፥ ሊገድል ወይም ሊያድን ይችላል። የፈቀደውን ካላደረገ እግዚአብሔርነቱ ወዴት አለ? እግዚአብሔር እኛ የወደድነውን ያለማድረጉ (ለምሳሌ ያለመፈወሱ) ጨካኝ አያደርገውም። ደግሞ ቢሆንስ? ቢጨክንስ ማን ይቆጣዋል? ማን ይከለክለዋል? ያለመፈወስን ከመጨከን ጋር የሚያያይዘው የኛ ጠባብ አስተሳሰብ እንጂ እርሱ ምንን ለምን እንደሚያደርግ ማን መርምሮ ይደርስበታል?

ከላይ እንዳየነው ከእርግማን በታች በወደቀች ዓለም ነው የምንኖረው። ቅዱስ ቃሉ እንደሚያስተምረን አማኞችም እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ከአካላዊ ስቃይ ሙሉ በሙሉ ነፃ አይወጡም። የክርስቶስ ምጽአት ጌታ ምድራዊ አካላችንን ሙሉ በሙሉ የሚዋጅበት ጊዜም ነው። (ሮሜ.8:19-25) አካላችንም ሙሉ በሙሉ የሚዋጀው የትንሳኤ አካል ስንለብስ ነው። ይህ የውጪው ሰውነት የሚጠፋና የሚበሰብስ ያኛው ደግሞ የማይጠፋ ነው። (2ቆሮ.5) የአማኞችን ስጋዊ ስቃይ ለመመልከት ከብሉይ ኪዳን ኢዮብን ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ጳውሎስን እንይ።

የዚህ የስህተት ትምህርት አስተማሪዎች በኢዮብ የደረሰበትን መከራና ስቃይ እራሱ በፍርሃቱና 'አፍራሽ ንግግሩ' በላዩ ያመጣቸው ነገሮች ናቸው ይላሉ። ለዚህም የሚጠቀሰው ኢዮ.3:25 ነው። ነገር ግን በኢዮብ ላይ የሆነው እንዲሆን የፈቀደው ሌላ ማንም ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነው። ምንም እንኳ የሆኑት ነገሮች እንዲሆኑ ያደረገው ሰይጣን ቢሆንም ነገሮቹ እንዲሆኑም ሆነ ሰይጣን እንዲያደርግ የፈቀደው ልዑል እግዚአብሔር ነው። ይህን እውነት

እንኳን እኛ የተገለጠውን መጋረጃ የምናይ አንባቢዎች እንቅርና ኢዮብ ራሱ እንኳ መረዳት የሚችለውን ያህል ተረድቶ ነበር። ስለዚህም ኢዮብ እጅግ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ይዘን እንጂ ከታማኝነቱ ጥቂትም ፈቀቅ አላለም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስስ? በ2ቆሮ.12:7-9 ጳውሎስ ስለ ስጋው መውጊያ ይናገራል። ይህ የስጋ መውጊያ አንድ ወይም ሌላ ዓይነት ሕመም መሆኑን እንረዳለን እንጂ ምን ዓይነት በሽታ መሆኑን አናውቅም። ክርስቲያን መታመም የለበትም እንደሚሉ አስተማሪዎች ሕመም የሚመጣው ከኃጢአት፥ ከእፍረሽ ንግግርና ካለማመን ከሆነ የጳውሎስ ችግር የትኛው ይሆን? በእጁስ ብዙዎች ሐዋርያዊ ተአምራት ተደርገው (ፈውስም ጭምር) እርሱ ግን ለምን ታማሚ ሆነ? ለምንስ የእግረ መንገድ አገልግሎትም ቢሆን ሐኪሙ ሉቃስ አብሮት እየዞረ እስኪያገለግል ድረስ አስፈለገ? ይህ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያውቅ ድንቅ አገኙ ጋይ ለሕመሙ መወገድ ለምን ከአንዴም ሦስቴ መጸለይ አስፈለገው? ሦስቴ ጸልዮ ለምን አልተፈወሰም? ስለ ጢሞቴዎስ የሆድ ሕመም በቃል ፈንታ የወይን መድኃኒት ማዘዙ ባለማወቁ ነው? (1ጢሞ.5:23) ጥሮፊሞስንስ ታሞ በሚሊጢን የተወው ያልተረዳው ነገር በመኖሩ ነው? (2ጢሞ.4:20) አፍሮዲጡስ ስለምን ታሞ ለሞት ቀረበ? (ፊል.2:27) በጊዜው የፈውስ ስጦታ ስላልነበረ ነው? ወይስ ለዘመናችን የእምነት አስተማሪዎች የተገለጠላቸው ጳውሎስ ያላወቀው ነገር ኖሮ ነው?

ኃጥአን ያልታመሙት ኃጥአን ስላልሆኑ አይደለም። ናቸውና። ጻድቃንም ቢታመሙ ጻድቃን ስላልሆኑ አይደለም። ናቸው። ጽድቃችን በኛ ሁኔታ ወይም በራሳችን የሚደረግ አይደለም። ክርስቲያኖች ችግር ወይም ሕመም ቢገጥማቸው እንደ ኢዮብ ወዳጆች በፍርድ በትር እንደብድባቸው በወቀሳና በማንኳሰስ ድንጋይም እንውገራቸው። ከነርሱ የተሻለ እምነት አለን የምንል ከሆነ እምነታችንን ወደ ሜዳ እናውጣው ጸልየንላቸው ይፈወሱ ወይም ተግባራዊ በሆነ መንገድ እንደግፋቸው እንጂ እምነታቸውን አንናቀው። አንፍረድባቸውም።

መድኃኒትን ያለመውሰድ ሌላው የ'ፈውስ' አስተማሪዎች የሚያበረታቱት ትምህርት ነው። መድኃኒትን መውሰድን ልክ በሽታውን አሜን ብሎ የመቀበልና ከበሽታውም ጋር የመተባበር ምልክት አድርገው ይወስዱታል። ከዚህም ትምህርት የተነሳ በጣም ቀላል በሆነ ሕክምና ሊድኑ እየቻሉ የተሰቃዩ፥ ኮማ ውስጥ የገቡና የሞቱም ሰዎች አያሌ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ መድኃኒት መውሰድን ይከለክላል? መድኃኒት መውሰድ ደካማነት፥ ኅጾሎነት፥ ያለማመን ነው ይላል? መድኃኒት መጠቀምና በሐኪም መታየት ኃጢአት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ እንኳን ይህን

ማድረግ ኃጢአት መሆኑን አይነግረንም። ማቴ.9:12፤ ማር 2:17 እና ሉቃ.5:31 ባለጤና ያልሆኑ ባለመድኃኒት እንደሚያስፈልጋቸው ይነግረናል። ይህ ጌታ ራሱ የተናገረው ነገር ነው። እየተናገረ ያለው ምሳሌ ቢሆንም በምሳሌው ውስጥ እውነትን ነው እየተናገረ ያለው። ስለዚህ ሐኪሞች ሠራተኞች እንጂ የሰይጣን መሳሪያዎች እንዳልሆኑ ከቃሉም እንረዳለን። ሐኪሞችም ቢፈውሱን እነርሱን ተጠቅሞ የፈወሰን እግዚአብሔር መሆኑን በማሳሰብ ጆን አር.ራይስ የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑር ሲጽፍ፤

> በመጀመሪያ መታመናችን በሰው ሳይሆን ሁሌም በእግዚአብሔር መሆን እንዳለበት እናስታውስ። እግዚአብሔር ሐኪሞችን ሊጠቀም ይችላል ተጠቅሞም በሽታን ሊያድን ይችላል። ብዙ ጊዜ ያለ ሐኪም፥ ያለ መድኃኒትም በጸሎት ብቻም ይፈውሳል። የሆነ ሆኖ በየትኛውም ቢሆን በሐኪምና ያለሐኪም ወይም በመድኃኒትና ያለ መድኃኒት በእግዚአብሔር መደገፍና እርሱ ለስጋችን ጥንቃቄና ለሕመማችን ፈውስ የሚያዘጋጅልንን መፍትሔ ልንቀበል ይገባናል። ...ማስጠንቀቂያው በአጭሩ ይህ ይሁን ሁሌ ችግራችንን ወደ ጌታ ዘንድ ማቅረብ አለብን። አንዳንድ ጊዜ ምሪቱ ሐኪም ወይም መድኃኒት ወይም አፕሬሽን መሆን እንዳለበት ግልጽ ይሆንልናል አንዳንዴም ሌላ መፍትሔ ይኖረዋል፤ ነገር ግን ሁሌም መታመናችን በእርሱ ዋናው አሳባችንም የእርሱን ፈቃድ አውቀን እርሱን ማስደሰት ይሁን።[34]

ኢሳ.1:6 እና ሉቃ.10:34 በቁስሎች ላይ ስለሚቀባ ስለሚያለዝብ ዘይት ይናገራል። ኢሳ.38:21 ነቢዩ ኢሳይያስ የበለስ ጥፍጥፍ አምጥተው በንጉሡ በሕዝቅያስ እባጭ ላይ እንዲለጥፉና እንደሚፈወስም ተናገረ። በኤር.8:22 "በገለዓድ የሚቀባ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ሐኪም የለምን? የወገኔ ሴት ልጅ ፈውስ ስለምን አልሆነም?" ይላል። የተናገረው ስለ መንፈሣዊ ፈውስ ቢሆንም ገለዓድ በዚያ ዘመን ብዙ መድኃኒቶች የሚሰሩባትና የሚቀመሙባትም ስፍራ ነበረች። (ኤር.46:11) ከማር.15:23 እንደምናነብበው ደግሞ ከርቤ የተቀላቀለበት የወይን ጠጅ እንደ ማደንዘዣ በመሆን ስቃይን እንደሚቀንስ ይታያል። በ1ጢሞ.5:23 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለሆዱ ሕመም ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲወስድ ነገረው። በማቴ.9:12 እና ሉቃ.4:23 ጌታ ስለ ባለመድኃኒት መጥቀሱ በጊዜው ይህ የሐኪሞች ተግባርና የሕክምና ሙያ የተለመደ መሆኑን ይነግረናል። የጳውሎስ የቅርብ አባሪ አገልጋይ የነበረው ሉቃስ ሐኪም ነበር። ቆላ.4:14 'ባለ መድኃኒት' ይለዋል። ከምሳ.17:22 እንደምንገነዘበው ደግሞ ስነ-ልቡናዊ መድኃኒት መኖሩንም አይሁድ ሳያስተውሉ አልቀሩም። ከዚህም

ባሻገር አይሁድ እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑንም ያውቁ ነበር። እግዚአብሔር ፈዋሽ እግዚአብሔር ነው። (ዘፀ.15:26) ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ማመን ሕክምናን ያለመቀበል ማለት አይደለም ወይም መታከም ማለት እግዚአብሔርን መካድ ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን ትቶ ባለመድኃኒቶችን ብቻ በመፈለግ አሳ ተሳስቶ ነበር። (2ዜና.16:12) የአሳ ስህተት ባለ መድኃኒቶችን መፈለጉ ሳይሆን እግዚአብሔርን ያለመፈለጉ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች እንደምናነብበው እግዚአብሔር ያለ መድኃኒት እንደሚፈውስ ሁሉ በመድኃኒትም ይፈውሳል። ስለዚህ መድኃኒትን መውሰድ ማለት መፈወስ የማይችለውን እግዚአብሔርን መርዳት ማለት አይደለም ወይም ኃጢአት አይደለም።

አንዳንድ የፈውስ ጉባዔዎች በሚደረጉበት ጊዜና ከመደረጋቸው በፊት የፕሮግራሙ ዜና በስፋትና በጥንካሬ ይሰራጫል። ብዙዎችም ሕሙማን እንዲጸለይላቸው አገር አቋርጠው ሳይቀር ይመጣሉ። እግዚአብሔር የሚፈውስም አምላክ ነውና የሚፈወሱ ይኖራሉ። ይህ ግሩም ነገር ነው። ይሁን እንጂ የአንዳንዶቹ ሕመምተኞች ፈውስ ስሜታዊና እዚያው በስብሰባው ቦታና ሞቅታ ያውም ለቅጽበት ብቻ የሚሆን ሲሆን ትንሽ ቆይተው መማቀቅ ይጀምራሉ። የአንዳንዶቹ ደግሞ ምንም እንኳ የሚጸልዩላቸው ሰዎችም ሆኑ እነርሱም ራሳቸው መፈወሳቸውን ደጋግመው ቢናገሩም ፈውሱ ያልመጣላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እንዲህ ካሉት ሰዎች ከፊሉ የእምነታቸውን ጎዶሎነት ሲያማርሩ ከፊሉ ደግሞ በአምላካቸው አማርረው እምነታቸውንም ይጥሉታል። በየትኛውም መንገድ ግን "ድናችኋል...ፈውሳችሁን ተቀበሉ" ያሏቸው ሰዎች ከተጠያቂነት ነፃ ይሆናሉ። ላለመፈወስ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱት የፈውስ ስጦታ አለን የሚሉት ሰዎች ሳይሆኑ የበሽተኞቹ ጎዶሎ እምነት መሆኑ በብዙ ማስረጃ ሊረጋገጥ ይሞከራል። በአዲስ ኪዳን እንደምንመለከተው ግን እግዚአብሔር ከፈቃዱ የተነሳ ያልፈወሳቸው ሰዎች ቢኖሩም ፈውስንና እምነትን ካጣበቅናቸው ዘንድ ያለመፈወስን የምናነብበው ከበሽተኛው ሳይሆን ከሚጸልዩት ሆኖ እናገኘዋለን። (ማቴ.17:14-21) በዚህ ክፍል እንደምናየው ይህ ሰው ያልተፈወሰው ከራሱ ሳይሆን ከጸላዮቹ እምነት ጎዶሎነት የተነሳ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው ሰው በጅማ ስበሰባዎች ላይ ስለሚገለጡ ፈውሶች አወዛጋቢነት ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፤

> በፈውስ ስብሰባዎች ስለሚሰጡ አስቀድሞ የታቀዱ ስነ-ልቡናዊ ነገሮች ማለትም ሰዎች ሊፈወሱ እንደሚችሉ፣ እንደሚፈወሱ እና እንደተፈወሱም እንዲያምኑም ስለሚደረገው ነገር ብዙ መዘርዘር ይቻላል። አስታውሱ

> ፈውሶች የሚደረጉት ሁሌም መዝሙር ባለበት፥ ብዙ ስሜታዊ ነገሮች በሚገለጡበት፥ የእግዚአብሔር ኃይል የግድ በሚባልበት፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሌም ፈውስ መሆኑ በሚነገርበት ወዘተ. የጉባዔ አገልግሎት ነው። ብዙዎቹ የሰላላቸው ፈዋሾች ትልልቅ አዩኝ ባዮች ናቸው። እየታየ ያለው በያዕ.5:14-16 እንደተሳለው ያለ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደቤታቸው ወይም ወደ ሆስፒታል አልጋቸው ጠርተው ለበሽተኞች እንዲጸልዩ የተባለው ጸጥተኛ አገልግሎት አይደለም። እየተፈለገ ያለው ይህ ሳይሆን በስሜታዊ ደስታ መሞቅ የትልቅ ጉባዔ ስነ-ልቡና እና የናፍቆትና የምኞት መገንባት ነው።[35]

ለበሽተኞች መጸለይ ጌታ ያዘዘውም ያስተማረውም ብቻ ሳይሆን መፈወስ እርሱ ምሳሌያችን በመሆን ያደረገውም ነው። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑ የማይካድ እውነት የመሆኑን ያህል በአንጻሩ ደግሞ በጌታና በፈውስ ስም የሚደረጉ መስመር የሳቱ ነገሮችም መኖራቸው ገሃድ ነው። ከቅርቦቻችን እንኳ ጥቂት ሰዎችን ብንጠይቅ ተጸልዮላቸው የተፈወሱ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ድናችኋል ተብለው በእርግጠኝነት የተነገራቸውና ያልተፈወሱ ሰዎችም አሉ። እንዲያውም ፈውስ ከታወጀላቸው በኋላ ከጥቂት ሰዓታት እስከ ጥቂት ቀናትና ሳምንታት ቆይተው የሞቱ ጥቂት ያይደሉ አሉ። የዚህ ዓይነቱ ነገር በጌታም ሆነ በሐዋርያቱ ተደርጎ ከሆነ የት ነው የተጻፈው?

(ማር.8:22-26 ዕውሩን ሰው ጌታ ከፈወሰው በኋላ ጠየቀው። መጀመሪያ ጌታ እጁን በጫነበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ አጣርቶ አላየም ነበር። ጌታ ሲጠይቀውም እውነቱን ከመናገር አልተቆጠበም ነበር። ሰዎችን እንደ ዛፍ ማየቱን ባይናገር ሰዎችን ከዛፎች ለይቶ የማየት ጤንነት ባልተሰጠውም ነበር። ጌታ ይህን ሰው ባንዴ መፈወስ ተስኖት አልነበረም ደረጃ በደረጃ የፈወሰው ምናልባት ለደቀ መዛሙርቱ ሊያስተምራቸው የወደደው ነገር ኖሮት ይሆናል። ዛሬ አንዳንዶች (በቁጥር ጥቂት ያልሆኑ ማለትም ይቻላል) የፈውስ ስጦታ አለን የሚሉ ወይም አላቸው የሚባሉ ሰዎች ለሕሙማን ከጸለዩ በኋላ በሽታው መጥፋቱትና ያለመጥፋቱን ለማረጋገጥ ስለ ሕመማቸው መጠየቅን አይወዱም ብቻ በደፈናው እንደ ተፈወሱ መናገርና በሽታው እንደሌለ መቁጠር እና ማስቆጠር ይቀልላቸዋል። ነገር ግን ጌታ እንዳደረገ ፈውስን ለማረጋገጥ አንድ ወይም ሌላ ነገር ማድረግ ድንቅ ነገር ነው። የጌታ ፈውስ የተረጋገጠ ፈውስ ነው። እዚያውና ወዲያው ወይም እየሄዱ እንደተፈወሱት ለምጻሞች ብዙ ሳይቆይ የሚደረግ ነው። በማቴ.8:16 ጌታ ያደረገውንና በሐዋ.5:16 ሐዋርያት ያደረጉትን ስናስተውል ሁሉ እንደተፈወሱ እናያለን።

በአንዳንድ የፈውስ ስብሰባዎች የሚፈወሱ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። ከተፈወሱትም የአንዳንዶቹ ፈውስ አካላዊ ሳይሆን ስነ-ልቡናዊ ብቻ ነው። የተፈወሱ እንዲመስላቸው ይደረጉና እውነትም ይመስላቸዋል። ነገር ግን ስነ-ልቡናዊ ፈውስ አካላዊ ፈውስ መምሰል እንጂ መሆን አይችልም። በእንዲህ ያሉ ስብሰባዎች ሞቅታና ግለት ወቅት በስሜት መወሰድና ያልሆነው የሆነ የሚመስልበት ሁኔታ ይኖራል። ጌታም ሆነ ሐዋርያቱ በመላ-ምት አልነበረም ፈውስን ያደረጉት። የዘመናችን አንዳንድ አገልጋዮች ግን በነሲብ ነው በሽታውንም ፈውሱንም የሚናገሩት። በሽተኛው የተቀመጠበትን ቦታም ሆነ የበሽታውን ዓይነት በመሰለኝ መናገር የተለመደ ነው። 'በስተግራ በኩል እመጨረሻ አካባቢ የተቀመጥክ ወይም የተቀመጥሽ...ግራ ወይም ቀኝ ጆሮህ ገደማ...በስተ ጎንህ በኩል የሚያምህ ወይም የሚያምሽ...' ወዘተ. ይባላል። ይህ መላ-ምት እንጂ መገለጥ አይደለም። ለነገሩ "መገለጥ" የሚባል የጸጋ ስጦታም የለም። አንዳንዶቹ አገልጋዮች ደግሞ የጉባዔ ፈውስ አገልግሎት ሲያካሂዱ የሚታዩና የሚታወቁ በሽታዎችን ስም አይጠሩም መኖራቸውም ሆነ ፈውሱም የማያስታውቀውን በሽታ ብቻ ነው ደጋግመው የሚጠሩት። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአንድ ዓይነት በሽታ በቀር የሚያውቁም አይመስሉም። ልክ በጥቂት በሽታዎች ላይ ልዩ ስልጠና የወሰዱ ዶክተሮች ይመስል ሁሌ ቢጠሩ እርሱን ነው። ሌሎች ደግሞ የሚፈውሰው እግዚአብሔር ሳይሆን ሲጸለይ የሚባለው ነገር እየመሰላቸው የፈውስ ቀመር በመከረጅ ሰዎችን በተለይም አማኞችን ያወናብዳሉ። በተለይ በመከረጅ የሚመጣው ጣጣ ብዙ ነው።

አንዳንድ የፈውስ አገልጋዮች በዚህ አገልግሎት ረገድ ከረር ያለ አቋምና ራቅና ጠምዘዝ ያለ አዝማሚያ ይወስዳሉ። በዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ እንደ ጀመሪና መሪ የሚታየው ቻርልስ ፎክስ ፓርሃም ሰማያዊ ፈውስ የሁሉም አማኝ መብት እንደሆነ አስተምሮ ነበር። አንዳንድ አስተማሪዎች የመንፈሳዊ ሰዎች መታመም ግራ ሲገባቸው ሌሎችም በሰይጣን ያመካኛሉ። ሌሎች በሽታን እንደ ኃጢአት በሽተኞችን እንደ ኃጢአተኞች ይቆጥራሉ።

ሆባርት ፍሪማን የተባለ መጀመሪያ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረና በ1960ዎቹ ካሪዝማዊ ንቅናቄ የተወሰደ ሰው ነው። ይህ ሰው በአሜሪካ አገር በኢንዲያና ግዛት የእምነት ጉባዔ የተባለውን ቤተ ክርስቲያን ጀመረ። በርሱ እምነትና ትምህርት መሠረት ሕክምና ከጥንታዊ ጥንቆላ የመነጨ በመሆኑ መድኃኒት መውሰድና ሐኪም ቤት መሄድ ለሰይጣን አሰራር መጋለጥ ነው። ስለዚህ የርሱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሐኪም የላቸውም ሴቶች ሲወልዱ እንኳ ሆስፒታል አይሄዱም። በቤት ውስጥ መውለድ በአገራችን የተለመደ ቢሆንም ይህ ግን አሜሪካ ነው! ከዚህ የተነሳ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መመስረት እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊታከሙና ሊድኑ

የሚችሉ ከመቶ የማያንሱ ሰዎች ሞተዋል። በአንዲት የ15 ዓመት ልጃገረድ ሞት ምክንያት ወላጆችዋ በግድየለሽነታቸው ተከስሰው የ10 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸው ነበር። ራሱ ሆባርት ፖሊዮ ከሚባል የእግር በሽታ ተፈወስኩ ቢልም በዲሴምበር 1984 ሲሞት በሳምባ ምችና እየባሰበት ከሄደው ከእግሩ ሕመም ጋር በተያያዘ የልብ መድከም ተጠቅቶ ነበር። ሆባርት የተጎዳው ከሕመሙ ይልቅ በራሱ ትምህርት ነበር ማለት ይቻላል።

ዛሬም ይህን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች በብዙ የሚቆጠሩ ናቸው። በርግጥ ከሆባርት በፊት ሌሎችም ፈውስ የክርስቲያን መብት መሆኑን ያስተማሩና የፈውስ ስጦታ እንዳላቸው የተናገሩ የነበራቸውም ግን በሕመም ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎች አሉ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጣም ዝነኛ የሆነው የፈውስ አገልጋይ ዊሊያም ብራንሃም በ1965 የመኪና አደጋ ደርሶበት ስድስት ቀናት ታሞ ሲሞት ተከታዮቹ ብራንሃም እንዲፈወስ ጸልየው አልሆን ማለቱ ሳይታከታቸው ከሞተ በኋላ ከሞት እንዲነሳም ጸልየውለት ነበር። ሌላው አገልጋይ ኤ.ኤ.አለን በ1967 በጉበት በሽታ ነበር የሞተው፥ ይጠጣ ነበርና። ካትሪን ኩልማን ወደ 24 ዓመታት ያህል ስታገለግል ቆይታ በ1976 ሞተች። በምታገለግልባቸው ጊዜያት የልብ ድካም ነበረባት። ሩት ካርተር እስቴፕልተን (የጂሚ ካርተር እህት)የፈውስ አገልጋይ ሆና ስታገለግል ኖራ ካንሰር እንዳለባት ስታውቅ ለመታከም ፈቃደኛ አልነበረችም፤ በ1983 ሞተች። በዚህም ዘመን በመሰል አገልግሎት የተሰማራው ጆን ዊምበር የልብ ታማሚ ሲሆን መታመሙን አልካደም መድኃኒትም ይወስዳል። በቴክሳስ የእምነት ፈውስ አገልጋይ የነበረው ጃክ ኮው 'ፈውስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፥ ያለመፈወስም ከእምነት ጎዶሎነት ብቻ የሚመጣ ነው' በማለት ሲያስተምር ቆይቶ ራሱ በፖሊዮ በሽታ ታሞና በሆስፒታል ውስጥ ቆይቶ በ38 ዓመቱ ነበር የሞተው።

ይህን ክፍል ስናጠቃልል የበሽታንም ምንጭ በትንሹ እንይ። በሽታ ሁሉም ከሰይጣን አይደለም የሚመጣው። ወይም ካለማመን አይደለም የሚወለደው። ከተለያዩ ምንጮች ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሊመጣብን ይችላል። የበሽታን ምንጭ ማወቁ ለመጠንቀቅም ሆነ ለመከላከል ይረዳናል። ጥቂቶቹ ከታች የምናያቸው ናቸው።

1. <u>የተፈጥሮ ሕግን መጣስ</u>። ለምሳሌ አንድ ሰው ከስድስተኛ ፎቅ በረንዳ ላይ ልክ መሬት ላይ እንዳለ አድርጎ ቢራመድ ወድቆ ይሰበራል ወይም ይሞታል። የተፈጥሮን ሕግ ማለትም የመሬት ስበትን ሕግ ስለጣሰ። ወይም አንድ ሰው ከመጠን በላይ እየሰራ በቂ እንቅልፍ ባያገኝ ይታመማል። አካል በተፈጥሮው እንዲያርፍም ተደርጎ ነው የተሰራው።

2. <u>የኃጢአት ውጤት</u>። እግዚአብሔር አታድርጉ የሚላቸውን ነገሮች በመተላለፍ ሰዎች በአካላዊ፥ አዕምሯዊና መሰል በሽታ ሊጠመዱ ይችላሉ። ለምሳሌ "አታመንዝር" የሚለውን ትዕዛዝ የተላለፈ አንድ ሰው ዝሙት-ወለድ የሆነ ደዌ ሲላማ መሆኑ አይቀሬ ነው።

3. በንዝህላልነት። ለምሳሌ ጤንነትን በሚጎዱ ንጽህና በጎደላቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያለ ምንም ጥንቃቄ መቆየት ወይም በቂ ልብስ ባለመልበስ ለብርድ መጋለጥ።

4. በውርስ ከወላጆቻችን የሚመጣብን። አንዳንድ ሕመሞች ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፉ መሆናቸው ግልጽ ነው።

5. ሰይጣን ሊያመጣብን ይችላል። (ሉቃ.13:10-17 በተለይ ቁ.16) ጌታን የሚያውቁትን ሁሉ ሰይጣን የሚጎዳበት ስልጣን የለውም። ከኢዮብ መጽሐፍ እንደምንመለከተው ግን የተፈቀደለትን ያህል ብቻ ሊያደርግ ይችላል።

6. የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ። በዮሐ.9:3 እንደምናገኘው ያ ሰው ዕውር ሆኖ የተወለደው ደቀ መዛሙርቱ እንደገመቱት እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት ስለሰሩ ሳይሆን የጌታ ክብር እንዲገለጥ ነው። ሰውየውም ሆነ ወላጆቹ ኃጢአት የሌለባቸው ንጹሐን ናቸው ማለት አይደለም ግን ሕመሙ የዚያ ውጤት አልነበረም። የዕውሩ ዓይኖች ስለበሩ የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ መታየቱ ግልጽ ነው። የአንዳንድ ሕመም ውጤቱ ቢመስለንም ባይመስለንም የጌታ ክብር ነው። 'እኔ እየተሰቃየሁ ጌታ እንዴት ይከብራል?' ልንል እንችል ይሆናል፤ ቁም ነገሩ መከበሩን ማወቃችን እንጂ እንዴት እንደሚከብር መረዳታችን አይደለም። ለኛ በማይገቡን ነገሮች ጌታ እንዴት እንደሚከብርና በየትኛው ይበልጥ እንደሚከብር መጨነቅ የራሱ ስራ ነው መሆን ያለበት።

ቻርልስ ሃሚል የተባለው ጸሐፊ ስለፈውስ አገልግሎት ሲጽፍ ኢሳ.53:5ን ጠቅሶ የሚከተለውን አሳብ ይሰነዝራል።

> በዚህ (ጥቅስ) መሠረት እምነታቸውን በመለማመድ ቅጽበታዊ ፈውስን እንዲያገኙና ከዚያ በኋላ የሕመሙ ምልክቶች መኖራቸው ቢቀጥልም እንኳ በዚያው እንዲቀጥሉ ይስተማራሉ። ስለ ሕመሙ ምልክቶች መቀጠል መጨነቅ እንደ ጎዶሎ እምነት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። እንዲያውም በስቃይ ውስጥ ያለ ሰው ፈውስን ከማግኘት ይልቅ ያገኘውን ለመጠበቅ ይበልጥ እምነት እንደሚስፈልገው ይነገረዋል።

በዚህ ረገድ የሚመጣው ጉዳት በብዙ መንገድ የሚገለጥ ነው። ካልጠፋው የሕመም ምልክት ችግር ጋር መታገሉ የወንጀለኝነትና የጭንቀት ሸክም ይፈጥራል። 'በእውነት ድኛለሁ? ከሆነስ የሕመሙ ምልክቶች ለምን ይኖራሉ? ሐኪም ማየት አለብኝ?' በሚል አሳብ ይወዘወዛል። በመካከሉ ደግሞ ሕመሙ ጥንቃቄ ሳይደረግለት በመቀጠሉ ምልክቶቹ ይብሳሉ። ተስፋ በመቁረጥ ሐኪም እስኪታይና ሐኪሙም ምንም ዕርዳታ ሊያደርግ እስከማይችል ይደረሳል። በሽተኛው በመጨረሻ የሕክምና መስመር ውስጥ ሲገባም እምነትን እንደካደና እግዚአብሔር የሰጠውን 'ፈውስ' እንቢ እንዳለ እንዲሰማው ይደረጋል። ባልጠፋው ሕመሙ ላይም የአጥፊነት ሸክም ይጨመርበታል። የጸጋ ስጦታ መሆን የነበረበትም ነገር በውሸት እምነት የተባለ የሃይማኖት ስራ ይሆናል። እንዲህ ያለው ሕመምተኛ በመጨረሻ ወደእነርሱ ሲመጣ ሐኪሞች 'የእምነት ፈውስ' ስለሚባለው ነገር መጥፎ ቃላት ቢናገሩ አያስገርምም።

የደኅንነት የመጨረሻ ዓላማ እኛን ሙሉ ማድረግ ቢሆንም የኢሳ.53:5 ዓውድና አባባል የሚያመለክተው የኃጢአታችንን ስርየት ነው። በተጨማሪም ቅጽበታዊ ፈውስ የክርስቲያን መብት መሆኑን ወይም ፈውስን ከመቀበል ይልቅ ማቆየቱ የበለጠ እምነት እንደሚጠይቅ አዲስ ኪዳን አያስተምርም። እግዚአብሔር በርግጥ በጤንነት በኩል ይቆማል ነገር ግን ብዙ ጊዜ የማንረዳቸው ችግሮች ሙሉነታችንንም ሆነ ቅድስናችንን ያደናቅፉታል። በተጨማሪም አንድ ሰው በተአምር ሲፈወስ ምልክቶቹ በሙሉ እንደሚጠፉና ሁሉም ደግሞ እንደሚያውቁት መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርገዋል። ሽባው ተነሳና ምንጣፉን ተሸክሞ ወጣ፤ ማንም ሊይዘው ያልቻለው የጌርጌሴኖን ዕብድ ፀጥ ብሎ ተቀመጠ ለበሰና ደህናም ሆነ። ፈውሳቸውን ለመጠበቅ እምነታቸውን የተለማመዱበትን ምንም ምልክት አናይም።[36]

ለማጠቃለል ፈውስ በቃሉ ውስጥ ያለ እውነት በመሆኑ የፈውስ ስጦታ ባላቸው አገልጋዮችም ሆነ በያዕ.5 መሠረት በሽማግሌዎች ዘይት መቀባት አማካይነት ለሕሙማን መጸለዩ ተገቢ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው። ጸልዮ ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተውም መደረግ ያለበት ነገር ነው። በአንጻሩ ደግሞ ሰዎች ባይፈወሱ እንኳ ይህን ፈርቶ መጸለይን ያለመተው አስፈላጊ ነገር ነው። የሰዎችን እምነት በፍርድ ዱላ መደብደብ ግን በቃሉ ውስጥ ያየናቸው አገልጋዮች ያላደረጉት በዘመናችን እየታየ ያለ አዲስ ዓይነት 'አገልግሎት' ነው። ይህን አጉል ዱላ በፍርሃትና በለዘብታ ማለፍ የለብንም። ምክንያቱም

ይህ የሰዎችን እምነት የሚያፈርስ የሰዎች ብቻ በትር እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም።

## የተአምራት ቀውስ ("ሦስተኛው ሞገድ")

ይህ ሦስተኛው ሞገድ የሚባለው ንቅናቄ ከዚህ በፊት በዚህ ምዕት ዓመት መጀመሪያ በቶፒካውና በአዙሳው ንቅናቄዎች አካባቢ ይታወቅ ከነበረው 'ሦስተኛው ልምምድ' ከሚባለው የተለየ ነው። በዚያን ጊዜ ሦስተኛው ልምምድ ይባል የነበረው አንደኛው ደኅንነት ሁለተኛው ቅድስና ሲሆን ሦስተኛው ልምምድ የሚባለው የመንፈስ ቅዱስ 'ጥምቀት' ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሁለተኛ ቡራኬና ሦስተኛ ልምምድም ተደርጎ ቢስተማርም ቅድስና ጣልቃ የገባው በጊዜው የቅድስና ትምህርት ተስፋፍቶ ይሰበክበት የነበረ ዓቢይ ርዕስ በመሆኑ ነው።

ሦስተኛው ሞገድ ከ1970ዎቹ በኋላ የተጀመረና እስከ ዘመናችንም ድረስ ያለ ንቅናቄ ሲሆን ቃሉን መጀመሪያ የቀመረው ፒተር ዋግነር የተባለው የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምሁር የነበረው ሰው ነው። ዋግነር በቦሊቪያ ሚስዮናዊ ሆኖ ለ16 ዓመታት ያገለገለ በኋላም በታወቀ የሥነ-መለኮት ሲሚናሪየም የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምሁር የሆነ ሰው ነው። እንደ ዋግነር አባባል የመጀመሪያው ሞገድ የበዓለ ኀምሳው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የዚህ ዘመን መጀመሪያ ካሪዝማዊ ንቅናቄ ሲሆን ሦስተኛው በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ እየሰራ ወይም ሊሰራ ያለው እንቅስቃሴ ነው። ይህን እርሱ የቀመረውን ንቅናቄ ካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ ብለው ሰዎች እንዲጠሩት ዋግነር አይፈልግም። ምክንያቱ የቃሉ ጥላቻ ሳይሆን በነዚህ ንቅናቄዎች ውስጥ የሚደረጉት መስመር ያለፉ ልምምዶች ብዙዎችን በማስደንገጥ አፍራሽነት ያለው ስሜት በመፍጠራቸው ነው።[37] የዚህ ንቅናቄ ማዕከላዊ ጭብጥ ድንቅና ተአምራትን አጥብቆ መፈለግና እነዚህ ነገሮች ለወንጌል ስርጭት ያላቸው ሚና ጉልህ በመሆኑ እርሱ የሌሉበት ወንጌል ጎዶሎ እንደሆነ እስከማሰብና ማስተማር መድረስ ነው።

> የሦስተኛው ሞገድ ተከታዮች ሐሴታዊ ልምምዶችን፥ ምስጢራዊ ክስተቶችን፥ ተአምራዊ ኃይሎችንና ተፈጥሮ-አለፍ ምልክቶችን አጥብቀው ይከታተላሉ በአንጻሩም ለተለመዱት በመንፈሳዊ ሕይወት የማደጊያ መንገዶች ማለትም ለጸሎት፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ ለቃሉ

ትምህርት፥ በመታዘዝ ለመጽናትና ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረትን ለማድረግ አነስተኛ ግምት ይሰጧቸዋል።[38]

ይህ ንቅናቄ በመሠረቱ ስሙ ብቻ ተለወጠ እንጂ በባህርዩ ከዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ በምንም የተለየ አይደለም። እንዲህ ያለውን ትምህርት በሚያስተምሩባቸው አብያተ ክርስቲያናት በነፃነት በማምለክ ስም እንግዳ ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ ስም ደግሞ ሰው ሰራሽ ድርጊቶች መፈጸማቸው ይስተዋላል። የሚታዩ አካላዊና ቁሳዊ ድንቆች ተአምራትና ምልክቶች ካልኖሩበት ያ ክርስትና ክርስትና ነው ሊባል አይገባውም ይላሉ 3ኛ ሞገደኞች። ወንጌል ሲሰበክ ተአምር መኖር አለበት ተአምር ሲያዩ ነው ሰዎች በሚገባ የሚለወጡት በማለት ተአምራትንና ምልክቶችን ለመውለድ እስኪያምጡ ይደርሳሉ። ይህ የመጨረሻው አሳብ በተለይ ጆን ዊምበር በተባለውና ከንቅናቄው መሪዎች አንዱ በሆነው ሰው በሰፊው ተዘክሯል።[39]

በሌላ አነጋገር 3ኛው ሞገድ የተአምራትና የምልክቶች ንቅናቄ ሊባልም ይችላል። ተአምራትና ምልክቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እውነታዎች ናቸው። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳናት ውስጥ ታይተዋል። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተአምራትን ማድረግ ከጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ ሆኖ የተሰጠ ጸጋ ነው። ይህን ጸጋ በአጉል መንገድ መለጠፍና በሌለበት እንዳለ ማስመሰል ችግር ይፈጥራል፤ ስህተትም ነው። የትኞቹም የጸጋ ስጦታዎች በተገቢው መንገድና በፈሪሃ-እግዚአብሔር ካልተያዙ ሊበላሹና በማነጽም ፈንታ ላያንጹና ብለውም እንዲያውም ሊያፈርሱም እንደሚችሉ ይህም ስጦታ ተመሳሳይ ጽዋ ሊደርሰው ይችላል። በየዋህነት ሲታይ ተአምራትና ምልክቶች እምነትን የሚፈጥሩ ይመስላሉ። በርግጥ ተአምራት አይተው ለጊዜው ያመኑና የተከተሉ ሰዎች እንዳሉ እንረዳለን። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን ስንመረምር ግን ተቃራኒውን እውነት ነው የምንረዳው።

እምነት ከመስማት ማለትም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ ተአምራትን ከማየት አይመጣም። (ሮሜ.10:17) በብሉይ ኪዳን በፈርዖን ፊት ብዙ ተአምራት ተሰሩ። ነገር ግን የፈርዖን ልብ እንደ ባልጩት ጠጠረ እንጂ አልለሰለሰም ነበር። እስራኤልም በምድረ በዳ ምንም ብዙ ተአምራት ቢያዩ የሚበሉት መብልና የሚጠጡት መጠጥ እንኳ በተአምር ቢሰጣቸው ነገር ግን ባለማመናቸውና ባለመታዘዛቸው ጠንቅ በምድረ በዳ ወድቀው ቀሩ እንጂ ወደ ተስፋዋ ምድር አልገቡም። (1ቆሮ.10:5፤ ዕብ.4:6) እሳት ከሰማይ ቢወርድ እንኳ ኤልዛቤልንና ሠራዊቷን ማሳመን አልተቻለም።

ጌታስ እኒያን ሁሉ ከዚያ በፊት ተደርገውም ተስምተውም የማይታወቁ ተአምራት አድርጎ ሰቀሉት ወይስ አመለኩት? በዮሐ.11 አልዓዛር ከሞት

የተነሳበትን ታሪክ እናነብባለን። በዮሐ.11:47-53 እንደምንመለከተው ተአምራቱ በተሰራበት በዚያው ቀን ሊገድሉት ተማከሩ። ድንቆች፥ ምልክቶችና ተአምራት እምነትን እንደማይፈጥሩ ዮሐ.12:37-38 እንዲህ ብሎ ያጠቃልልልናል፤ "ነገር ግን ይህን ያህል ምልክት በፊታቸው ምንም ቢያደርግ ነቢዩ ኢሳይያስ ጌታ ሆይ ማን ምስክርነታችንን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ? ብሎ የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ በእርሱ አላመኑም።"

የ3ኛው ሞገድ ንቅናቄ ተከታዮችም ሆኑ አስከታዮች ከቃሉ ይልቅ በልምምድ ላይ ያተኩራሉ። ስለ እምነት፥ ስለሚያስተምሩት ክርስቲያናዊ ትምህርታቸውና ኑሯቸው ሲጠየቁ መመሪያቸው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ቢጠቅሱም በተግባር ግን የሚጋጭ ነገር ያደርጋሉ ወይም ቃሉን ያስተምሩና ቃሉ የማይላቸውን ይለማመዳሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ስልጣን ያለው አዳዲስ መገለጥን መቀበል አንዱ እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ልምምድ ነው። ልምምድ ስህተት የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ቃሉ ግን አንዴም ስህተት የሚሆንበት ጊዜ ጨርሶ የለም። ልምምድን በቃሉ ሳይሆን ቃሉን በልምምድ ከፈተንነው እስህተት ማጥ ውስጥ መውደቃችን የታወቀ ነገር ነው። ሌላው እዚህ ቦታ ሳይባል መታለፍ የሌለበት እውነት ከአካላዊና ከሚታዩ ተአምራት ሁሉ የሚበልጠው ትልቁ ተአምር የኃጢአተኛ ሰው ንስሃ መግባትና የእግዚአብሔር ልጅ መሆን እንደሆነ ነው። በሰማያት በመላዕክትም ዘንድ ትልቅ ሐሴት የሚደረገው ተራራ ሲነደል ወይም ሽባ ሲተረተር ሳይሆን ኃጢአተኛ ንስሃ ገብቶ ዳግም ሲወለድ መሆኑ ከሁሉ የሚበልጠውንና ልናተኩርበት የሚገባንን ተአምረ-ተአምራት ያመለክተናል። ሌላው ትልቅ ተአምር አንድ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚኖረው የተቀደሰ የየዕለቱ የክርስትና ኑሮ ነው።

ጠቅለል ሲደረግ ሦስተኛው ሞገድ ድንቅንና ተአምርን ከመራብና ከመጠማት ምልክትንም በመሻት መሠረት ላይ የቆመ ንቅናቄ ነው። በተጨማሪም 'መስራት አለበት ወይም ከስራ ጥቅም ላይ መዋል አለበት' ከሚሉ ፍልስፍናዎች (ማለትም pragmatism እና utilitarianism) ድርና ማግ የተሰራ ይመስላል።[40] ጸሮችና ፈሪሳውያን ከጌታ ዘንድ ምልክትን በፈለጉ ጊዜ ጌታ ምልክት ሳይሆን ጠንካራ ተግሳፅ ነበር የሰጣቸው። ምልክትን የሚሻ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ነው። (ማቴ.10:39) ለማመን ምልክት የግድ አያስፈልግም። እምነት የማናየውን የሚያስረዳ ነገር ነው እንጂ በማየት ምርኩዝ የሚደገፍ አይደለም፤ (ዕብ.11:1፤ 2ቆሮ.5:6-7) ማየትና ማመን አብረው አይሄዱም። ማየት ካለ ማመን አይኖርም የሚታመነው ነገር ታይቷል! መለኮታዊውን እውነት ማመን ካለ ደግሞ ማየት የግድ አስፈላጊ አይደለም።

ይህ ማለት እግዚአብሔር ተአምራትን ላያደርግ እጁን አጣምሮ የተቀመጠ አምላክ ነው ወይም ተአምራት ሲደረጉ ሁሌም ሰይጣን እንዳደረገ ሁሉ በጥርጣሬ ልናይ ይገባል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ዛሬም በልጆቹ የወደደውን ያደርጋል። ያ ባይሆን ተአምራትን የማድረግን ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ባልሰጠም ነበር። ተአምራት በእግዚአብሔር አሰራር ውስጥ ተገቢ ቦታ አላቸው። የእርሱንም ባህርይ የሚያንፀባርቁ ናቸው። በሐዋርያት ወይም በእግዚአብሔር መልዕክተኞች እጅ ይህ ቢፈጸም እነዚህ በእውነት የጌታ መልዕክተኞች የመሆናቸው ማስረጃም ነው። ተአምር ልክ ብርሃን የእሳት እራትን እንደሚስብም ያለ የመስህብነት ባህርይ አለው። የሚሳቡትም ደግሞ ተአምሩን አይተው ቢሳቡም እምነት የሚፈጥረውን የእግዚአብሔር ቃል ሰምተው ሊድኑ ይችሉ ይሆናል። ተአምር ግሩም ነገር ቢሆንም የእምነት ፋብሪካ ግን አይደለም ወይም የእምነት ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ተአምራት ደግሞ በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በሰይጣንም ሊሰሩ እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም። ሰይጣን የመንፈስ ፍሬዎችን ነው ሊሰራቸው የማይችል እንጂ ተአምራትን ድንቆችን ምልክቶችንና የጸጋ ስጦታ የሚመስሉ ችሎታዎችንስ አስመስሎ ይሰራቸዋል። በማቴ.24 በመጨረሻው ዘመን የሚነሱ ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሳዊ ክርስቶሶች ቢቻላቸውስ ያመኑትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ምልክቶችንና ተአምራትን እንደሚያደርጉ ጌታ አስጠንቅቋል። ስለዚህ ተአምር የመጨረሻው ዘመን ምልክትም መሆኑንና በክርስቶስ ስምም እንደሚደረጉ አውቀን ጠንቃቃ መሆን ያስፈልጋል።

## የሐብት ቀውስ

ከዘመናዊው የተቃወሰ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ብዙ የስህተት መልኮች አንዱ 'የሐብት ወይም የብልፅግና ወንጌል' የተባለው ነው። ይህ ማለት በአጭሩ፥ አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የናጠጠ ሃብታም መሆን አለበት ችግር የሚሉት ነገር ወደ እርሱ ቀርቶ ወደ አካባቢው መድረስ የለበትም። ሐብት የትክክለኛ ክርስትና ምልክት ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሐብት ስለሆነ ድኅነት ኃጢአት ነው። የሚል ነው። ይህ ትምህርት በዙዎች ንቅናቄውን እንዲደግፉና እንዲያራግቡ አድርጎታል። ቢሆንም አያስገርምም፤ ሐብትን ማግኘትን ማን ይጠላል? ኃብታም ለመሆን አቋራጭ መንገድ ይመስላልና ሳይለፉ ከተበለጸገ ለምን ይለፋል? ይህ ትምህርት በተለይ ስጋዊ ክርስቲያኖችን የመሳብ ጉልበት አለው። አንዳንዶቹ አገልጋዮች እውነትም ሲከብሩ ይታያል ነገር ግን እኒህ ከሌሎች ኪስና ቦርሳ በሚወጣው እየከበሩ መሆናቸውን

አይቀበሉም።ሊቀበሉም አይፈልጉም። ለመሆኑ ገንዘብ ምንድር ነው? ገንዘብ በጤናማ ተፈጥሮው በራሱ የገለለ (neutral)ነገር ነው። በጥበብ በተግባር ላይ ቢያወሱት ብዙ ገንቢ ነገሮችን መስራት የሚችል ባሪያ ነው። ከዚህ ጎድለው ቢሻረኩት መጥፎ ጌታ መሆንም ይችላል። ይህንም አልፎ ላላጤኑት የእግዚአብሔርን ቦታ መውሰድ የሚችል አምላክ መሆን ይችላል። ለዚህም ነው ጌታ በማቴ 6:24 ላይ ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማይቻል ከተናገረ በኋላ "ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም" ያለው።

ከላይ ከተመለከትነው የተሳሳተ ትምህርትና ድምዳሜ ተቃራኒ የሆነ ብዙም እንደትምህርት ያልተዛመተ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ተቀባይነት ያለው የተሳሳተ አመለካከት አለ ያም "ክርስቲያን ሰማያዊውን እንጂ ምድራዊውን ንብረት ከቶም መፈለግ የለበትም እውነተኛ ክርስትና ምድራዊውን ኑሮ በድኅነትና በምስኪንነት መግፋት ነው" የሚል ነው። ይህም እንደዚያኛው ሁሉ ያፈነገጠ ድምዳሜና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የወጣ ስህተት ነው። ሐብት የእግዚአብሔር ሰዎች ዋና ዓላማ መሆን የለበትም። ዋና ዓላማችን መሆን ያለበት የእግዚአብሔር ክብር ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ክርስቲያኖች ንዋይን ዋና ዓላማቸውና የመጨረሻ ግባቸው በማድረግ በዚህ መስመር ርቀው ይሄዳሉ።

ይህ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ሦስት ዐሥርት አልፈውታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገራችን በሰረገ ጊዜ አንዳንድ አስገራሚ ነገሮችም ተደርገው ነበር። ለምሳሌ አስር ባለ አንድ ብር ኖቶችን አመሬት ላይ ደርድረው ባለ መቶ ብር ኖቶች እንዲሆኑ ሁለት ወንድሞች ለረጅም ጊዜ ተንበርክከው ጸልየው ነበር። እግዚአብሔር የአገር ምጣኔ-ኃብትን የሚያቃውስ ያልተመዘገበ ገንዘብ እየሰራ የሚያድል ሸፍጠኛ ያለመሆኑን በየዋህነት አልተረዱትምና። ይህን ማድረግ የጌታ ባህርይ አይደለም።

ይህ ትምህርት የሚጠቅሳቸው ዐውደ ወጥ የሆኑ ጥቅሶች አሉ። በጣም ተዘውትረው ከሚጠቀሱት ሁለት ክፍሎች ውስጥ አንደኛው በዘፍ. 12 የሚገኘው የአብርሃም በረከት ነው። አብርሃም እግዚአብሔር ሳይጠራው ደኃ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም። በርግጥ ከተጠራ በኋላ ይበልጥ በልጥጓል በስጋም ተባርኳል። በረከትን የስጋና የሃብት ብቻ ማን አደረገው? ከአምልኮተ ጣዖት ወደ ኅያው አምላክ ዘወር ማለትና ለሌሎችም ደኅንነት ምክንያት የመሆን ዕፁብ ሰማያዊ በረከት ጊዜያዊ ከሆነ ምድራዊ ባርኮት አይበልጥምን? ሁለተኛው ጥቅስ ደግሞ ሚል. 3:7-12 ያለው ነው። ይህን ክፍል ገንጥለን በማውጣት ሳይሆን ከዐውዱ ጋር እንየው። ከጠቅላላው መጽሐፍ እንደምንረዳው አይሁድ ከምርኮ ምድር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው

መደላደል ጀመሩ። በተለይ በዚህኛው ክፍል እንደምናየው ደግሞ አስራታቸውን መክልከል ይዘዋል። አስራት ከሙሴ ጀምሮ የተደነገገ የሌዋውያን ቀለብ ነው። (ዘሌዋ. 27:30-34፤ ዘዳ. 14:22-27) እኒህ ሌዋውያን ቀለብ ሲያጡ ወደ እርሻ ወደ ንግድና ወደ ሌላ ሙያ መሰማራታቸው አይቀሬ ነው። ይህ ከሆነ ቤተ መቅደስ ወና መሆኑ መንፈሳዊውም እንቅስቃሴ መታጎሉ ነው። አስራት በብሉይ ኪዳን መፈጸም ያለበት ሕግ እንጂ ለበረከትና ለማትረፊያ ተብሎ የሚሰጡት ዋና አይደለም። በአዲስ ኪዳንም ለወንጌል እንቅስቃሴ የምንሰጠው ስጦታ ከልብ የመነጨ መስዋዕት እንጂ በአቋራጭ የመበልጸጊያ ሎተሪ አይደለም። የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች ከነዚህ ዋና ከሚባሉ ጥቅሶች ሌላ አንዳንድ ሰው ሰራሽ ሕግጋትም ያስተምራሉ። እነዚህ አስተማሪዎች ከአዲስ ኪዳንም የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች አሉ።የመጀመሪያው ማቴ. 19:29 ነው። ይህ ጥቅስ ከላይ ከቁጥር 16 ጀምሮ የተያያዘ ነው። ይህን ክፍል ጠንቅቀን ብንመለከት የመበልጸጊያ መንገድ ሳይሆን እንዲያውም ለባለጠጎች ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ሆኖ እናገኘዋለን። ከቁጥር 29 ሁለት ነጥቦች ማየት አስፈላጊ ነው።

-የመጀመሪያው መተው ነው። ይህ "መስጠት" ከሚባለው ነገር የተለየና የጠለቀም ነው።

-ሁለተኛው መቀበል ነው። ይህ ደግሞ ውጤት ነው፤ ምላሽ ነው። ነገር ግን እንዴት ሚስት የተወ መቶ ሚስቶች መጠበቅ እንደሚገባው ይህ ክፍል አያስተምርም።

ሌላው የአዲስ ኪዳን ክፍል ደግሞ ገላ. 6:7 ነው። ይህም ጥቅስ ብቻውን ሳይሆን ቢያንስ ከ7-10 ያለው ሳይለያይ መወሰድ አለበት። ይህ ክፍል ዐውዱን በጥሞና ካጤንነው በስጋ ዘርቶ መበስበስንና በመንፈስ ዘርቶ የዘላለም ሕይወትን ስለማጨድ እንጂ ለእግዚአብሔር ጥቂት ገንዘብ ሰጥቶ ብዙ መቀበልን ፈጽሞ አያስተምርም።

ዲ.አር.ማኮኔል በጻፈው መጽሐፉ ይህን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች የብልጽግናውን ተስፋ በሁለት ቦታዎች እንደሚያደርጉት ይናገራል። አንደኛው የቃል-እምነት አስተማሪዎች እንደሚያስተምሩት የመሰለ መንፈሳዊ ወይም የእምነት ህግ አለ። በዚህ ህግ ውስጥ ንዋይንም የሚመለከት ሕግ አለ። የዚህን ሕግ አሰራር ማወቅ የብልጽግና ቁልፍ ነው ይላሉ።ይህን የሚያስተምሩት ብዙ የመበልጸጊያ ቀመሮችንም እየቀመሩ ያስተምራሉ። እየተለማመዱም ያለማምዳሉ። ሁለተኛው የመበልጸጊያ ተስፋ ግን ግልጽ ከሆነ ጥሬ ስግብግብነት የመነጨ ትምህርት ነው። ይኸኛው ደግሞ ሰባኪው ሰዎች ማለትም ምዕመናን የእርሱን አገልግሎት በመደገፍና ለማንቀሳቀስ የገንዘብና

ለገንዘብ ቦርሳህ ተናገር 'አንተ ትልቅ ወፍራም በገንዘብ የተሞላህ ቦርሳ' በለው።ለባንክ ደብተርህ ተናገር። 'አንተ የባንክ ደብተር አንተ የኔ ከሆንክ ጀምሮ እንደዚህ ኃብታም ሆንህ አታውቅም? በገንዘብ ታጭቀህ የል እንዴ?' በለው" ብላለች።[43]

ይህ በጥንታዊም ሆነ በዘመናዊ ጥንቆላዎችና በምስራቃውያን ኃይማኖቶች የተለመደ አሰራር ነው። እኒህ አስተማሪዎች ጌታችንም ሆነ ሐዋርያቱ ድህነትን ከቶ እንደማያውቁም ይናገራሉ። ኢየሱስ የለበሰው እጀ ጠባብ በጊዜው የኃብታሞች ልብስ እንደነበርና ስለዚህም ቱጃር እንደነበር ጳውሎስን ደግሞ የቄሳር ባለስልጣኖች ጉብ እንዲሰጡት ስለተመኙት የቄሳር ወኪል ለመግለጽ ከተመኘው ኃብታም የመሆኑ ምልክት እንደሆነም ያስተምራሉ። ጌታ የሰማይና የምድር ጌታ ስለሆነ በርግጥ የጸጋ ጌታ ነው ለኛ ሲል የሆነው ግን ከዚህ የተለየ ነው። የጌታን ብልጽግና ለማየት አንዱን የወንጌል መጽሐፍ ብቻ ማንበብ በቂ ነው። ሲወለድ በበረት ሲቀበርም በተውሶ መቃብር ነው። በመካከልም የነበሩት ጊዜያት ከዚህ የራቁ አልነበሩም። ጳውሎስም መከራ እየቆጠረ በእጁ ድንኳን እየሰፋ አልፎ አልፎም አብያተ ክርስቲያናት በሚልኩለት የፍቅር ስጦታ ነበር ወንጌልን ያሰራጭ የነበረው። ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው ብልጽግናን ሳይሆን "ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና እንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም። ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል" የሚል ዓይነት ነው። (1ጢሞ.6)

በፕሮቴስታንት ተሃድሶ ዋዜማ ዮሃን ቴትዝል በተባለው ካቶሊካዊ ቄስ አማካይነት ይሸጡ የነበሩ 'የይቅርታ ማስገኛ የስርየት የምስክር ወረቀቶች' (indulgence) ነበሩ። ለገዢው እንዲሁም በተለይ ለሙታን ከሲዖል ወጥቶ ወደ ገነት መግቢያ ተብሎ ነበር ይህ የስርየት የምስክር ወረቀት የሚገዛው። ሽያጩ በከፊል የዕዳ መክፈያ በከፊል ደግሞ ሮም ለሚሰራው የቅዱስ ጴጥሮስ ሕንፃ ወጪ መሸፈኛ ሲሆን ዮሃን ገቢውን ለማስገኘት የእግዚአብሔርን ቃል ምንም የማያውቁትን ምዕመናን እንዲገዙት ማነሳሳት ጀመረ። ሲናገርም "የገዢዎቹ ሳንቲም የሳንቲም ማስቀመጫው ውስጥ ገብታ ድምጿ ቅጭልጭል ብሎ ሲሰማ በስቃይ ቦታ ያለችው ነፍስ ወዲያው ብርር ብላ ወጥታ ወደ ገነት ትገባለች" ይል ነበር። ከዚህ ንግድ ጀርባ የሮማው ጳጳስ ኃይልና ስልጣን ስላለ በቀላሉ መጋፋት የሚቻል አልነበረም። ለተሃድሶው ዋናው ምክንያት ይህ ባይሆንም ማርቲን ሉተር ይኖር በነበረበት በዊተንበርግ አቅራቢያ ይህ ሽያጭ መካሄዱ አሳዝኖት አስቆጥቶትም ነበርና ሉተር "ዘጠና አምስቱ ቃላት" የተሰኘውን የመቃወሚያ ጽሑፉን በጥቅምት 1517 በሚያስተምርበት በዩኒቨርሲቲው የጸሎት ቤት በር ላይ ለጠፈው።

ይህ አሰራር የጊዜው ልማድ ነበር እንጂ በኋላ የመጣው ነገር እንዲመጣ የተደረገ አልነበረም። በነዚህ ቃላት ውስጥ ይህን የስርየት ንግድ የሚቃወሙ ነጥቦችም ነበሩ። በተለይ 27፥28፥45፥50፥51 እና 66 ሌሎችም ጥቅሶች ይህን ንግድ ይቃወማሉ። 27 እና 28 እንዲህ ይላል "እነዚህ 'ሳንቲም የመሰብሰቢያውን ሳጥን ስትነካ ነፍስ ከስቃይ ቦታ በቀጥታ ወጥታ ትበርራለች' የሚሉት የሰውን ፈጠራ እየሰበኩ ያሉ ሰዎች ናቸው። ሳንቲም የሳጥኗን ስር ስትነካ ስስትና ስግብግብነት እንደሚጨምር ግልጽ ነው። የቤተ ክርስቲያን ምልጃ ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው።" በቁጥር 45 ደግሞ የተቸገረ እንዲገዛ የሚደጉሙ የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሳቸው እየጠሩ እንደሆነ ይናገራል።"[44]

ይህ ወረቀት ባልተጠበቀ ሁኔታና ፍጥነት ተባዝቶ ብዙ አገሮችን አዳረሰ። በሉተር ላይ ትልቅ ክስ ተከፍቶበት አሳቡን እንዲቀይርና ንስሃ እንዲገባ ዕድል ቢሰጠውም ሉተር ግን ፍንክች አላለም። እንዲያውም ለሉተራዊ እና ብሎም ለፕሮቴስታንት እምነቶች ጥርጊያው ተከፈተ። ከአራት ክፍለ-ዘመናት ተኩል በኋላ ማለትም በዘመናችን በአዲስ ካባና ትንሽ በተቀየረ መልክ የብልጽግና ወንጌል መጣ። የተቀየረውም መልክ ነፍስ ከሲዖል ማውጣት ሳይሆን በምድር በብልጽግና ኑሮ መባረክ ነው።

ከዚህ ትምህርት 'ትልልቅ' አስተማሪዎች አንዱ ኦራል ሮበርትስ ይህን የብልጽግና ሕግ "የእምነት ዘር" ይለዋል። ይህም ለእርሱ አገልግሎት ማለትም ለኦራል ሮበርትስ የወንጌል ማህበር እንዲሁም በስሙ ለሚጠራው ዩኒቨርሲቲ ገንዘብን መርዳት ለድርጅቱም የገንዘብ ረብጣ መላክ በእምነት ያንን ዘር መዝራት ነው። ልክ የተዘራ ዘር ደግሞ በዝቶ እንደሚመረት ሰዎቹም ተትረፍርፎላቸው ይባረካሉ።[45] ይኸው ሮበርትስ በጥር 1987 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሚሰራው ተጨማሪ የሕክምና ሕንፃ ማሰሪያ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ስምንት ሚሊዮን ብር ካልተሰበሰበ እግዚአብሔር ወደ ቤቱ እንደሚጠራው ማለትም እንደሚሞት በመናገር የገንዘብ ስብሰባ ዘመቻ አድርጎም ነበር። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ገንዘብ ለመሰብሰብ ዮሃንም ሆነ ኦራል እንዳደረጉት ከቃሉ መስመር የወጣና ቅሌት ያለበትም ስራ ሲሰራ ያሳፍራል። የዓለም ምጣኔ-ኃብት እየተቃወሰ ኑሮም እየጠጠረ ሲመጣ አዱኛ ማግኘት ማለት ጥሩ መስህብነት ያለው ነገር ነውና ብዙዎች ወደዚህ የስህተት ትምህርት ቢሳቡ አያስገርምም።

አንዳንዶቹ አስተማሪዎች ገንዘቡን ለሚልኩላቸው ሰዎች የሆነ ዓይነት መታሰቢያ ነገር ይልካሉ። ከነዚህ መካከል ቁራጭ ጨርቅ ወይም መሃረብ (በቦርሳ ወይም በኪስ የሚያዝና ገንዘብ የሚያበረክት ይሉታል)፥ ሳሙና

(ከድህነትና ከችግር መታጠቢያ መሆኑ ነው)፥ የሰናፍጭ ፍሬ የሚሏቸውም አሉ (ለመበልጸግ እምነት እንደሚያስፈልግ ለማስታወስ መሆኑ ነው)፥ ሌሎችም ነገሮች ሊላኩ ይችላሉ። እነዚህ አስተማሪዎች ይህን የሚልኩትን ነገር "ነጥበ ተራክቦ" (point of contact) ይሉታል። ገንዘብ ሰጪውና ተቀባዩ የሚገናኙበት መሆኑ ነው። ይህ ጥንቆላ እንጂ ክርስትና አይመስልም። አይደለምም።

የእግዚአብሔር ቃል በግልጥ ብልጽግናን የስህተት አስተማሪዎች መርቢያ የሚያደርጉት ነገር መሆኑን ይናገራል። ይህ ትምህርት ሁሌም የስህተት አስተማሪዎች አንድ ገጽታ ነው። 1ጢሞ.6:3-19 ክርስትና መነገጃ እንዳልሆነ ኃብታም የሆኑ ሰዎችም እንዲያካፍሉ እንጂ እንዳይታበዩ ይናገራል። ይሁዳ.11 የሐሰት አስተማሪዎች ስለደመወዝ ለበለዓም ስህተት ራሳቸውን አሳልፈው እንደሰጡ ይናገራል። 2ጴጥ.2:1-3 እና 14-16 ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ይነግሩናል። በተለይ 2ጴጥ.2:3 "ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል" ሲል እራሳቸው በፈጠሩት ተረትና ወሬ ማለቱ ነው። እነዚህ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት አዳዲስ ነገርና ዘዴዎችም ከመፍጠር ወደ ኋላ አይሉም።

ከላይ እንደተመለከትነው 1ጢሞ.6 ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሚዛናዊ የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጠናል። እነሂም፤

- ፍቅረ ንዋይ የሀሰተኛ ትምህርቶች ባህርይ ነው (:3-5)
- ኑሮዩ ይበቃኛል ማለት የጤናማ ክርስትና ምልክት ነው (:6-10)
- ጤናማ በሆነ ብልጥግና ሀብታም የሆኑ ክርስቲያኖች ተስፋቸው በሀብት ሳይሆን በእግዚአብሔር እንዲሆንና በሀብታቸውም መልካም እንዲያደርጉ ይናገራል፤ (:17-19)

በተለይ በሦስተኛው ነጥብ ላይ ለማከል ያዕ.5:1-6 እንደሚነግረን ጤናማነት በጎደለው መንገድ ባለጠጎች የሆኑም ሊኖሩ እንደሚችሉ ነው።

ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት የምንሰጠው አስራትና በኩራት እንዲሁም ማናቸውም ዓይነት መባ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው እንጂ ወደ ባንክ ቤት እንደሚገባ ገንዘብ ወለድ መቀበያ መሆን የለበትም። ማናቸውም የክርስቲያን ገንዘብ ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ሲሰጥ ለቤተ ክርስቲያን ነው መሰጠት ያለበት እንጂ ለሰው መሆን የለበትም። ለሌሎች ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተጓዳኝ ለሆኑ የአገልግሎት ተቋሞች የሚሰጥ ስጦታን ቤተ ክርስቲያን ብትሰጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን በኩል ቢሰጥ ይህ ጥሩ ልምምድ ነው።

ማናቸውም ይህን መሰል ተቋሞች የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ የሚያራምዱ መሆናቸውንና ቤተ ክርስቲያንም የምትደገፋቸው መሆኗን ሲያውቁ ጥሩ የሆነ ግንኙነት ይኖራል።

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ መንፈሳዊ ድርጅቶች የሰዎችን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ምዕመናንን ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ከድርጅታቸው ጋር ሊያጣብቁ መጥፎ ሙጫ ይለቀልቋቸዋል። ምዕመናን ጌታ ልባቸውን እንዳነሳሳቸው እንዲህ ያሉ ድርጅቶችን ይርዱ፤ ይሁን እንጂ ማንነታቸውንና ዓላማቸውን፥ ግቦቻቸውንና ተጠያቂነታቸውንም ይመርምሩት። እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን እንድንሰዋለት የሚፈልጋቸው መስዋዕቶች አሉ፤ እነዚህም:- ሰውነታችን፥ ገንዘባችን፥ ምስጋናችንና አገልግሎታችን ናቸው። ገንዘባችንን እንደ መስዋዕት ስናቀርብ እንደ መስዋዕት ነው መሆን ያለበት እንጂ እንደ ሌላ መሆን የለበትም። የገንዘባችን መስዋዕት እግዚአብሔር ከባረከን በረከት ለእርሱ ስራ ማስኬጃ የምንሰጠው መሆኑን ማሰብም አለብን። ይህ የፍቅር ግዴታችን ነው እንጂ ግብር ወይም ኪራይ አይደለም። የምንሰጠውም እንዲሰጠን ሳይሆን ስለሰጠን ነው። የኛ ፈንታ መስጠት ነው መባረክ የእርሱ ድርሻ ነው። ክርስትና የሕይወት ግንኙነት እንጂ የጥቅም ሽርክና አይደለም። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ማንም ክርስቲያን በአቋራጭ ሐብትና ብልጽግናን በመፈለግ በተሰማራበት ስምሪት ታታሪና ትጉህ ሠራተኛ ሊሆን ይገባዋል። እንዲህ ያለው የስህተት ትምህርት ደግሞ ትጋትን ሽባ የሚያደርግ መርዝ በውስጡ አለበት። ደግሞም ክርስቲያን የሆነ ሰው (ከማንም ከመንግስትም ይሁን ከመሥሪያ ቤቱ ወይም ከሌሎች ሰዎች) በስርቆት የጎደፈ እጅ ሊኖረው አይገባም።

ጤናማ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም ሊኖረን ካስፈለገ እስካሁን ከተመለከትነው ስህተት በተቃራኒ አቅጣጫ ያፈነገጠውንም ሌላ ስህተት ማወቅና ከዚህም መጠንቀቅ ደግሞ ያስፈልጋል። ይህም ስህተት፥ "ክርስቲያን ሰማያዊውን እንጂ ምድራዊውን ንብረት ፈጽሞ መፈለግ የለበትም፥ ድሃ መሆን አለበት፥ እውነተኛ ክርስትና ምድራዊውን ኑሮ በምስኪንነት መግፋት ነው፥ ገንዘብ የክፋት ምንጭ ነው" የሚል ስህተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን የኃጢአት ሁሉ ሥር ገንዘብ ሳይሆን ገንዘብን መውደድ ነው። (1ጢሞ.6:10) በዚህ በ1ጢሞ.6 ይህ ገንዘብን መውደድ ከስህተት ትምህርት ጋር ተያይዞ የቀረበ ቢሆንም በአንፃሩ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ክርስቲያን ኃብታሞች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተናግሮ ኃብታቸውን እንዴት ማስተዳደር እንደሚገባቸውም ይናገራል (:17-19)። ኃብት በማጭበርበርና በማምታታት እንደሚገኝ ሁሉ በንጽህናና በትጋትም ይገኛል።

እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጥ አምላክ ነው።

ዳዊት "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም" ሲል እግዚአብሔር እያግበሰበሰ ሁሉን ይሰጠኛል ወይም የምፈልገውን ሁሉ ይሰጠኛል ማለቱ ሳይሆን <u>የሚያስፈልገኝን</u> ይሰጠኛል ማለቱ ነው። ይህ የእረኛ ባህርይ ነው። የምንፈልገውና የሚያስፈልገን አንድ አይደሉም። እግዚአብሔር በባህርይው መራጭ ነው። የሰማዩ አባታችን ሳንለምነውም የሚያስፈልገንን ያውቃል። (ማቴ.6:8 እና 25-31) እኛም በሚሰጠን ሁሉ ታማኞች ልንሆንና ከላይ ከተመለከትነው የስህተት ትምህርትም ልንጠነቀቅ ይገባናል።

## አዲሱ ቀውስ ('ቅዱስ' ሳቅ)

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙ የመነቃቃት ታሪኮች ተዘግበው ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ገንቢ ሲሆኑ ሌሎቹ የሚረብሹና የሚያውኩ ነገሮችን የተሞሉ ናቸው። አንዳንዶቹ ብልጭ ብለው ድርግም እንደሚል እሳት ናቸው፤ ደማቅ አይደሉም፥ ከአጥቢያይቱ ቤተ ክርስቲያንና ካሉበት ቀበሌም እምብዛም አያልፉም፥ አንዳንዶቹ ግን በተከሰቱበት ትልቅና ጥልቅ ለውጥ በመፍጠር ወደ ሌሎችም አካባቢዎች በመዛመት ወንጌል እንዲሰራጭና ነፍሳት እንዲድኑ አድርገዋል፥ ጌታም ከብሮባቸዋል። የነዚህ መነቃቃቶች አነሳሳቸው ብዙ ጊዜ ፍጹም ግብታዊ ቢመስልም ነገር ግን ከጀርባቸው እንደ ጀርባ አጥንት የጠነከሩ ምክንያቶች ይገኛሉ።

በጃንዋሪ ወር 1994 ማለትም በኛ አቆጣጠር በጥር ወር 1986 ዓ.ም. መጀመሪያ በካናዳ የምትገኘውን የቶሮንቶ ከተማ በኋላም የካናዳንና አልፎም በሌሎችም አህጉራትና አገሮች ያሉ ምዕመናንን ያወዛገበ ጉዳይ ተከሰተ። ከምእመናኑ አንዳንዶቹ ጉባኤውን የተካፈሉ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በመስማት ብቻ ነው የሚያውቁት። አንዳንድ ሰዎች ይህ ነገር ፈጽሞ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ይህን ነገር ሙሉ በሙሉ የሰይጣን አሰራር ነው ይሉታል፤ ሌሎችም ይህ በህልፈተ-ጊዜ ውስጥ የሚቀዘቅዝ ስሜታዊ ነውጥና የስጋ ሥራ ብቻ ነው ሲሉት አንዳንዶች ግራ ተጋብተውና 'ይህ ነው' ለማለትም ፈርተው በትዝብት ሲያዩት ቆይተዋል።

ይህ ከቶሮንቶ ካናዳ በመነሳት ተዛማች የሆነው ክስተት ገና ቀድሞውኑ በአንዳንዶች ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ለውጥን የፈጠረና በሌሎች ደግሞ መደናገርን ያስከተለ፥ በአብያተ ክርስቲያናትም ዘንድ በአንዳንዶቹ መነቃቃትን ሲፈጥር በሌሎቹ መረበሽንና መከፋፈልን የወለደ ነገር ሆኗል። ይህ ነገር እዚያው ሚሲሶጋ በሚባለው የቶሮንቶ ክፍል በሚገኘው ከአውሮፕላን

ጣቢያው ጋር በሚቀራረበው ወደ 350 ያህል አባላት በነበሩት የኤርፖርት ቪኒያርድ ክርስቲያናዊ ኅብረት (Airport Vineyard Christian Fellowship) ከሰማይ ዱብ ያለ ሳይሆን በዚህ ኅብረት ከተጀመረው አንዳንዴ "የሳቅ መነቃቃት" ሌላ ጊዜ ደግሞ "የደስታ ጥምቀት" ከተባለው ልምምድ (አሁን ንቅናቄ ሊባል ይችላል) ጀርባ የሆነ ነገር አለ። በርግጥ ከዚህ ቀደም ብሎ የተለያዩ አገልጋዮች በዚህች ኅብረት እየተገኙ ቢያገለግሉም የጥር 1986ቱ ግን የተለየ ነበር።

እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 20 ቀን 1994 የ A.V.C.F. ፓስተር ጆን አርኖት የአራት ቀናት ኮንፍረንስ አዘጋጅቶ ራንዲ ክላርክ የተሰኘውን በሴንት ሉዊስ፥ ሚዙሪ የምትገኘውን የቪኒያርድ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ተናጋሪ አድርጎ ይጠራዋል። ይህ ከመሆኑ ቀድሞ ራንዲ በትልቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ገብቶ ወደ መታወክ ቀርቦ ሳለ አንድ ወዳጁ አንድ ምክር ይለግሰዋል ያም ሮድኒ ሃዋርድ-ብራውን የተባለው ደቡብ አፍሪቃዊ አገልጋይ ኮንፈረንስ አዘጋጅቶ ወደሚያገለግልበት የኬንት ሄግን ወደሆነችው ወደ ሬማ መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ እንዲካፈል ይመክረዋል። ይህ ሃዋርድ-ብራውን ደቡብ አፍሪካዊ ዜጋ ሲሆን ወደ አሜሪካ ሚስዮናዊ ሆኖ ከመጣበት ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የአገልግሎት ማዕከል ከፍቶ ማገልገል የጀመረ ሰው ነው። ራንዲ ክላርክ ወደዚህ ስብሰባ ሄዶ ከተካፈለ በኋላ በጣም ደህናና ሌላ ሰው ሆነ። ሮድኒ ከጸለየለትም በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጣና ወደ አገልግሎቱ ተመለሰ ከዚያም በኋላ እርሱ የተለማመደውን ነገር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ማስተማርና በየአምልኮውም መደጋገም ጀመረ። ይህ ራንዲ ክላርክ ወደ ቶሮንቶ ከመጣ በኋላ እንደታቀደው አገለገለ፤ ነገር ግን ይህ የተጀመረው የአራት ቀናት ኮንፈረንስ በአራት ቀናት ማብቃቱ ቀርቶ በሳምንት ለስድስት ምሽቶች እየተደረገ ሳይቋረጥ መካሄድ ጀመረ ሳምንታትና ወራትም ተቆጠሩ። ብዙዎችም ከቅርብና ከሩቅ እየመጡ ተካፈሉት።

በነዚህ የኮንፈረንስ ቀናትና ከዚያም በኋላ የሚደረጉት የአምልኮ ጊዜያት ልዩ መታወቂያ ሰዎች መዝለላቸው፥ መንቀጥቀጣቸው፥ መገንደሳቸው (መውደቃቸው) ብቻ ሳይሆን ዋናውና ይህን ከሌሎች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ሳያቋርጡ ለረጅም ጊዜያት ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በመሆን መሳቃቸውና በተለያዩ ዓይነት የእንስሳትና የአራዊት ድምጾች (ለምሳሌ የውሻ፥ የአንበሳ ወዘተ.) መጮኻቸው ነው። በዚህች ቤተ ክርስቲያን 'መገንደስ' ወይም 'Slaying in the Spirit' የሚባለው ልምምድ ሌላ ስም ወጥቶለታል ያም 'የምንጣፍ ጊዜ' ወይም 'carpet time' ተብሎ ተሰይሟል። የተገነደሱ ሰዎች "የምንጣፍ ጊዜ እየወሰዱ ነው" ይባላል። አንዳንድ ጊዜም በመሰብሰቢያ ቦታው ያሉት ወንበሮች ተንቀሳቃሽ ከሆኑ ይነሱና አዳራሹ ለመገንደስ አመቺ ይደረጋል። ለአንድ ዓመት

ያህል "የቶሮንቶው በረከት" ወይም "'The Toronto Blessing'" እየተባለ በተለይ በሰሜን አሜሪካ መንፈሳዊ የዜና ማሰራጫዎች ሲጠራ፥ ሲነገርለትና ሲጻፍለት የቆየው ይህ ንቅናቄ "ቅዱስ ሳቅ" በሚል ሌላ መጠሪያ የሚታወቀው ነው። ሳቁ ብቻ ሳይሆን 'ቅዱስ ሳቅ' የተባለው ጩኸቱም 'ቅዱስ ጩኸት' የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ ርዕስና እንቅስቃሴ በምዕራቡ ዓለም መንፈሳዊዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ዓለማዊው መገናኛ ብዙኃንም እጅግ ያተኮረበት፥ የዘገበውና የተቸበትም ርዕስ ነው።

የChristian Research Journal የዊንተር 1995 ዕትም ሮድኒ ሃዋርድ-ብራውን ይህን ሳቅና ደስታ "የመንፈስ ቅዱስ ማደንዘዣ" ብሎ እንደሰየመው ዘግቧል፤ ደግሞም "ደስታ ድምጽ አለው፤ ያም ድምጽ ሳቅ ነው" ብሎ ተናግሯል።[46] ሮድኒ በፖርት ኤሊዛቤት፥ ደቡብ አፍሪቃ በጁን 12/1961 (እ.ኤ.አ.) ተወልዶ እዚያው ያደገ በ5 ዓመቱ ጌታን የተቀበለና በ18 ዓመቱም ማለትም በ1980 አገልጋይ የሆነ ሰው ነው። የመጀመሪያ አገልግሎቱ በነበረበት አካባቢ ባለው 'ወጣት ለክርስቶስ' (Y.F.C.) በሚባለው ድርጅት በትምህርት ቤቶች እየተዘዋወረ ሰራ። ከዚያም በጆሃንስበርግ 'የሬማ የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን' በምትባለው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገባና ተማረ። ከዚያም በኬፕ ግዛት በምትገኘው 'የእግዚአብሔር ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን' በምትባለው ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ለአምስት ያህል ዓመታት አገለገለና ወደ ነበረበት ት/ቤት ስራ ለመፈለግ ሄደ እዚያም ለሁለት ዓመታት አስተምሮ በ1987 መጨረሻ በሚስዮናዊነት ለማገልገል ወደ አሜሪካ መጣ። ከዚያም በታምፓ፥ ፍሎሪዳ የአገልግሎት ማዕከል ከፍቶ ማገልገል ጀመረ።

ወደ ቶሮንቶው የA.V.C.F. ቤተ ክርስቲያን ብዙዎች በተለይም መጋቢዎችና አገልጋዮች ከአውሮጳና ከሌሎችም አህጉራት ሳይቀር በመምጣት የመሳለም ዓይነት ጉዞ አድርገዋል። በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለፉት ሰዎች ስለሆንላቸው ነገር ሲናገሩ የእግዚአብሔር ፍቅር በጣም ጎልቶ እንደታያቸውና እንደተሰማቸው ለእርሱም ልዩ ፍቅር እንዳደረባቸው ይናገራሉ። ስሜታዊ ቅርርብ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ተሃድሶና የጠባይ ለውጥ አካላዊ ፈውስም ያገኙ አሉ። ብዙዎቹም ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያናቸውም የሚሆን ሰንቀው ነው የተመለሱትና ከመልስ ጉዞ ማግስት ጀምሮ በአንዳንዶች በታዎች ተመሳሳይ ክስተቶች ሲፈጸሙ በሌሎች ደግሞ የመሻከርና የመከፋፈል ምልክቶችና ውስጣዊና ውጪያዊም መከፋፈሎችም ተፈጽመዋል። አደገኛ አዝማሚያና ሰይጣናዊ አሰራር ነው የሚሉትም ይህን የመከፋፈል ነገር በመመልከት ነው። የካናዳው የመነቃቃት ኅብረት (C.R.F.) ይህን ንቅናቄ

በአትኩረት ተመልክቶታል።

> እንደ ካናዳው የመነቃቃት ኅብረት ዲሬክተር እንደ ሃሮልድ ሉትዘር አባባል የቶሮንቶው በረከት የእውነተኛ መነቃቃት ምልክቶች ይጎድሉታል። "ከታሪክ እንደምንረዳው መነቃቃቶች ለእግዚአብሔር ታላቅ የሆነ የአክብሮትና የፍርሃት ስሜትን ይጨምራሉ። ቀጥሎም ጥልቅ የሆነ የኃጢአት መወቀስና ንስሃን በማፍራት በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች መለወጥ የሚከተለው ግልጽ የሆነ ፍሬ ነው። 'መነቃቃት ጠልሉ እስኪታይ ድረስ መንከትከት ሳይሆን ሌላ ነገር ሁሉ ነው ማለት ይቻላል" ይላል ሉትዘር። 'በዚህ ንቅናቄ ውስጥ የእውነተኛ ንስሃ ስሜት አላይበትም።" [47]

በነዚህ የ'ቅዱስ ሳቅ' ጉባዔዎች ከሳቅ፥ ከማጓራትና ከተለያዩ የጩኸትና የድምጽ ዓይነቶች ብዛት የተነሳ መስበክ አይቻልም፤ ቢሰበክም ከሰባኪው በላይ ሁካታው ስለሚያይል በ1ቆሮ.12 እና 14 የተሰጠው መመሪያ ሲሰራ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ህልውና እውነተኛ ምልክት የሆነው ራስን መግዛት በተግባር ሲውል አይታይም። ብዙዎች ይህን ልምምድ በምሥራቃውያን ኃይማኖቶችና በስህተት ትምህርቶች ውስጥ ከሚገኙ ባህርያት ጋርም ያያይዙታል። ከዚህ በፊት በነበሩት ዘመናት አንድ ሰው በጉባዔ ውስጥ በአምልኮ ጊዜ ቢወድቅ፥ ቢርበተበትና ቢንቀጠቀጥ፥ ደረቱን ደግፎ ሆዱን እስኪያመው ቢስቅ፥ እንደ ቀበሮ ወይም እንደ ውሻ ቢጮህ፥ እንደ አንበሳ ቢያገሳ ወይም እንደ ሌሎች እንስሳትና አራዊት ቢያጓራ የቤተ ክርስቲያን አስተናጋጆች ወደ ሌላ ክፍል ወስደው ይጸልዩለትና አጋንንቱን ያወጡለት ነበር፥ ዛሬ ግን እነዚህ ነገሮች እንዲያውም የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ውስጥ የመኖሩና የመስራቱ ምልክት ተደርገው ሲነገሩና ሲለማመዱት ይህ የበግ ለምድ እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብና መጠየቅ እንዴት አይገባም? ያላመኑ ሰዎችም ወደ ጌታ ቤት የመታደምና ቃሉን ሰምቶ ወደ ደኅንነት የመምጣት ዕድል አላቸውና ደግሞም ለእነርሱም ወንጌልን የመናገር ኃላፊነት አለብንና። 'የማያምኑትስ ይህን ነገር እንዴት ይመለከቱታል?' ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው። 'የራሳቸው ጉዳይ፥ የተጠሩት እንደሁ መምጣታቸው አይቀርም የሚሰናከሉት ያልተጠሩት ናቸው' የሚል ያልበሰለ ምክንያት መስጠት ኃላፊነት ከሚሰማቸው ሰዎች የሚጠበቅ አይደለም። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለሰዎች ልብ የሚናገርበት ብዙ መንገድ ቢኖረውም ዋናው በዚህ ዘመን የሚናገርበት መንገድ ማለትም ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ባለው ነገር ከተሸፈነና ከደበዘዘ የደኅንነት መልዕክት እንዴት ሊተላለፍ ይችላል? የደኅንነትን መልዕክት ያለመስማት ብቻ ሳይሆን ያልሆነ ሌላ ነገር ሰምቶ መሄድስ ከእምነት መስመር አያርቃቸውም?

አንዳንዶች ተጠራጣሪዎች ለዚህ ንቅናቄ የሚሰጡት መልስ በሐዋ.5 የሚገኘው የገማልያል መልስ ነው፥ ያም "ይህ አሳብ ወይም ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና፥ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፤ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ።" የሚል ነው። በምዕራብ ቶሮንቶ የምትገኘው መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆነው ሪቻርድ ሆሊዴይ ይህን ጠቅሶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፥

> የገማልያል ምክር የፈሪሳውያን ጥበብ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኝ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በሚያሳዝን አኳኋን የቶሮንቶን በረከት በተመለከተ ብዙዎች የሚጠቅሱት ማስረጃ ጥቅስ ነው፤ "በጊዜ የመፈተንን ዕድል ስጧቸው፥ ቢከናወንላቸው ከእግዚአብሔር ጋር መጣላታችሁ ነው፤ ተመልካች ሁንና ልምምድህ አስተማሪህ ይሁን' ይባላል።
>
> የገማልያል አስተያየት ሰማዕትነትን አዘግይቷል ነገር ግን አስተያየቱ ያልዳነ የወንጌል ደጋፊ ያልሆነ ሰው አስተሳሰብ ነበር። ክርስቲያኖች "ለኃይማኖት እንዲጋደሉ" ተመክረዋል። (ይሁ.3) "መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ" ተብለናል። (1ዮሐ.4:1) የስብከት፥ የልምምድና የተግባርም ቀጥተኛነት መለኪያ ቁንቢያችን የእግዚአብሔር ቃል ነው። [48]

ከላይ የተጠቀሰውን ቃል የያዘው Faith Today የተሰኘው የካናዳ ወንጌላውያን ኅብረት መጽሔት በዚሁ ዕትሙ አንድ መንፈሳዊ መነቃቃት ከእግዚአብሔር የመሆኑ መለኪያዎች ምን መሆናቸውን ለማሳየት ጆናታን ኤድዋርድስ የተባለው ሰው 'ታላቁ መነቃቃት' በተሰኘው በ18ኛው መቶ በአሜሪካ በነበረው መነቃቃት ወቅት መጋቢና አገልጋይ የነበረው የጻፈውን ጠቅሷል። ጆናታን ኤድዋርድስ በዚህ ርዕስ ማለትም በመንፈሳዊ መነቃቃት ላይ በሰፊው የጻፈ ሲሆን የአስመሳይ መነቃቃቶችንም ባህርይ በስፋትና በዝርዝር ዘክሯል። አምስቱ የእውነተኞቹ መነቃቃቶች ምልክቶች፤

1. በሰዎች ዘንድ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም አዳኝ የመሆኑ

አክብሮት ይጨምራል።

2. ሰዎችን ከኃጢአት እንዲርቁና ወደ ቅድስና እንዲቀርቡ ያደርጋቸዋል።

3. ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን ፍቅር ይጨምረዋል።

4. በመሠረታዊ የእምነት እውነቶች ላይ ይመሠርታቸዋል።

5. እግዚአብሔርንና ሌሎችን ሰዎች ለማገልገል ትልቅ ፍቅር በውስጣቸው ይቀሰቅሳል።[49]

የእምነታችን መሠረትና መመሪያ ቅዱስ ቃሉ ከሆነ ይህንና የመሳሰሉትን ልምምዶችም የሚደግፍ ጠንካራ ድጋፍ ከቃሉ መጠቀስ አለበት። ለ "ቅዱስ ሳቅ" የሚሰጠው ማስረጃ ግን ሰብዓዊ ልምምድ ብቻ ነው። ልምምድ ደግሞ እምነትን የመደገፍ አቅም ስለሌለው ልምምዱም ተለማማጁም አንድ ቀን ሊወድቁ ይችላሉ። ስለዚህ ጠንቃቃ መሆንና በዓለቱ ላይ መመስረት እንጂ ያሚያልፍ ጎርፍ ጠራርጎ በሚወስደው አሸዋ ላይ መቆም የማያዋጣ ለአደጋ መጋለጥ ነው። በመንፈሳዊ መነቃቃቶች ወቅት እንደ ደራሽ ወንዝ በዝተው የሚጎርፉ ግን አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮች ይኖራሉ፤ አንዳንዴ ምዕመናን ዋና የሆኑትን በመተው ዋና ባልሆኑ ነገሮች ላይ በማተኮር ለኪሳራ ይዳረጋሉ፥ ካለመብሰል ማለትም በቃሉ ስር ካለመስደድ የተነሳም መወሰድ በሌለባቸው ነገር የሚወሰዱ ይኖራሉ ደግሞም ልታይ ባዮች አጋጣሚውን ለግል ጥቅምና ለመበዝበዣ ሊጠቀሙበት መሞከራቸው ዕውቅ ነው።

እግዚአብሔር አፍንም ልብንም ትርጉም ባለው ሳቅ የሚሞላ አምላክ ነው። ምንም እንኳ እያረሩ መሳቅ ቢኖርም፥ ውሸታም መገልፈጥ ቢኖርም፥ ማፌዝና በሌላው ጥፋት ላይ ማላገጥና ማላገድ ቢኖርም፥ ሳቅ የአካላዊና የውስጣዊ ደስታ ውጪያዊ መግለጫ ነው። አካላዊ ሲባል ለምሳሌ ኩርኮራን መውሰድ ይቻላል፥ ውስጣዊ ሲባል ደግሞ አዕምሮአዊና ስሜታዊ የሳቅ ምንጭን መውሰድ ይቻላል። ሌላ ዓይነት ሳቅም አለ ይህ መሳለቅ የሚሉት ነው፥ ከመጠን በላይ በራስ መታመን ወይም ደግሞ ንቀት አርግዞ የወለደው ሳቅ እንደማለት ነው። በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስም ይሁን በተለይ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና በምናገኝበት በአዲስ ኪዳን ስለ ሳቅ ብዙ የተጻፈ ነገር አናገኝም። በተለይ በአዲስ ኪዳን እጅግ ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ ነው ሳቅን በተመለከተ የምናገኘው። ይህ ማለት ክርስቲያን አይስቅም ፊቱም ሁሌ እንደ ላም ፊት ምንም ዓይነት ስሜት የማያመለክት ይሆናል ማለት አይደለም። ሰው ስጋ፥ ነፍስና መንፈስ ያለው ክቡር ፍጡር ነው። የውስጡን ስሜትም በቋንቋም ይሁን ያለቋንቋ የመግለጥ ችሎታ አለው። እንስሳትና አራዊትም እንኳ የደስታ

ስሜት አላቸው ይህንንም የሚገልጡበት መንገድ አላቸው፥ አንዱ መንገድ አንድ ወይም ሌላ ዓይነት ድምጽ ማውጣት ነው። ሰዎችም የውስጥ የደስታ ስሜታቸውን በፈገግታ፥ በሳቅ ወይም ተግባራዊ የሆነ ነገርን በማድረግ ይገልጣሉ።

መክ.3:4 ለመሳቅም ጊዜ እንዳለው ይነግረናል። መክ.7:3 "ከሳቅ ኀዘን ይሻላል" ይልና ምክንያቱን ይናገራል። በመዝ.2:4 (37):13 እና (59):8 እግዚአብሔር በጠላቶቹ እንዲስቅ ይናገራል። መዝ.(52):6 ጻድቃን በኀጥአ ጥፋት እንደሚስቁ ይናገራል። በዘፍ.17:17፤ 18:12-15 እና 21: 6 የአብርሃምንና ሳራን ሳቅ እናገኛለን፤ ለእነዚህ ባልና ሚስት ጌታ እውነተኛ ሳቅን አደረገላቸው። የ100 ዓመት አዛውንትና የ90 ዓመት አሮጊት እንኳን ትወልዳላችሁ ሲባል ይቅርና እንደ ተረት 'ወለዱ' ተብሎ ሲነገር እንኳ ያስቃል። እግዚአብሔር የሚሳነው የለምና እንዲህ ያለ ነገር ያደርጋልም በማድረጉም ያስቃልም። በእግረ መንገድ "ቅዱስ ሳቅ" ከእነዚህ የትኞቹን እንደሚመስል በማስተዋል ሌሎችን ስለ ሳቅ የሚናገሩ ጥቅሶች በመመልከት ስለምንና ስለየትኛው ዓይነት እንደሚናገሩም ተመልከቱ። 2ነገ.19:21፤ 2ዜና.30:10፤ ነህ.2:19፤ ኢዮ.5:22፥ 8:21 ፥ 9:23 ፥ 12:4 ፥ 22:19 ፥ 29:24 ፥ 41:21 ፤ መዝ.(22):7 ፥ (126):2 ('ደስታ' የተሰኘው ሳቅ የሚል አሳብ ያለው ነው።) ምሳ.1:26፤ ምሳ.14:13፤ መክ.2:2፥ 7:6 ፥ 10:19 ፤ ኢሳ.37:22፤ሕዝ.23:32። በአዲስ ኪዳን ሳቅ ወይም መሳቅ (ጌሎስ ወይም ጌላኦ) የሚለው ቃል ጥቂት ቦታዎች ነው የተጠቀሰው፤ ሉቃ.6:21 እና 25 ይህ ጌታ የተናገረው የወዮታና የብፅዕና ቃል ውስጥ የሚገኝ ትምህርት ነው። በማቴ.9:24 ማር.5:40 እና ሉቃ.8:53 ደግሞ የምኩራብ አለቃውን ብላቴና ሊያስነሳ ሲሄድ ብላቴናይቱ መሞቷን ያወቁት ሰዎች ጌታ ተኝታለች ሲላቸው የሳቁበት ሳቅ ነው። ሌላው በያዕ.4:9 የምናገኘው ለክርስቲያኖች የተሰጠ የማሳሰቢያ ቃል ነው።

የ 'ቅዱስ ሳቅ' እና 'ቅዱስ ጩኸት' ምንነት ጠጋ ብለን ስንመለከተው ከላይ ከተገለጡት የትኛው ክፍል ውስጥ እንደሚወድቅ መናገር አይቻልም፤ እንዲህ ያለው ያልተለመደ የጅማ ሳቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ስለሌለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ማለት አንችልም። ቅዱስ ቃሉ የማይደግፈውን ነገር ምንም እንኳ የሚስብ፥ የሚያስደስት፥ የሚያምርና የሚጥም ወይም ሌላም ሌላም ቢሆን በመንጠቆ ላይ ያለ የዓሳ መያዣ ምግብ ስለሚሆን ፈጥኖ መጉረሱ ቆይቶ መጎረስን ስለሚያስከትል ያለመጉረሱ ጥበብ ነው። ይህም ነገር እንዲሁ ነው። ቅጥ ያጣ ሳቅን ወይም ጩኸትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተደረገ ወይም ክርስቲያኖች ስላደረጉትም 'ቅዱስ' ብሎ መሾሙ ተገቢ አይደለም።

ክርስቲያን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ቅዱስ ካልነው ሌሎችም ክርስቲያኖች ለሚያደርጓቸው ነገሮች ሁሉ የፈቃድ ወረቀት እንደ መስጠት ያስቆጥራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ድጋፍና ማስረጃ የማናገኝላቸውን በዓለምና በሐሰተኛ ኃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ዓለማዊ ስነ-ልቡናዊና ሰይጣናዊም የሆኑ የሞላ ስሜት ማጉደያ ስልቶችን ክርስትና አስነስተንና 'ቅዱስ' ብለን የክርስትና ስም ሰጥተን የእምነታችን 'አበ-ልጅ' ማድረግ ስህተት ነው። በቀረቤታ ሲያዩት "ቅዱስ ሳቅ" ቅዱስም አይደለም ሳቅም አይደለምና ጠንቃቃ መሆኑ ይበጃል።

# የመደምደሚያ ቃል

እንዲህ ያለ መጽሐፍ ሲጻፍ ወይም በእንዲህ ያለ ርዕስ ላይ ይህን የመሰለ አስተያየት ሲቀርብ አንዳንድ አንባቢዎች ስለ መጽሐፉም ሆነ ስለ ጸሐፊው የተለያዩ አስተያየቶች ሊሰነዝሩ ይችላሉ፤ ይጀምራሉም። አንዳንዶች፥ አገልጋዮችም ጭምር፥ ርዕሱን ለማንሳትና ለመወያየትም ይፈራሉ። ግልጽ ያልሆንና ከዚህም የተነሳ ልዩነት የሚፈጥር ይመስላቸዋል። ነገር ግን ሁለቱም አይደለም። ልዩነት የሚፈጥረው ከሰዎች አሰራር እንጂ ከእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ያለመሆን የተነሳ አይደለም። በምዕራፍ አንድና ሁለት ውስጥ የተጻፉት እውነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ናቸው። ምዕራፍ ሦስት ታሪካዊ ቅርፅና ይዘት አለው። ምዕራፍ አራት ግን ከታሪክ አንጻርና በመጠኑም በዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚታዩት ነገሮች በመነሳት የተጻፈ ነው። የመጽሐፉ ዓላማ በትንሹም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና ሥራ መግለጥ፥ የጸጋ ስጦታዎችን ምንነት ማወቅና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጤናማ በሆነ መንገድ ማኅበረ ምዕመናን ሊገለገሉበት የሚችሉበትን መንገድ ለመጠቆምና አንዳንድ የተሳሳቱ ነገሮች በዚህ ዙሪያ የሚታዩ በመሆናቸው ይህንንም ለማሳየትና ሰዎችም በመንፈስ ቅዱስ ስም በሚያደርጉት ነገር ግን እርሱ የሌለበት የራሳቸው ብቻ ስራ ላይ አማኞች ዓይናቸውን እንዳይጨፍኑ ለማድረግም ነው። የሚያደርጉም እንዲታረሙና የተሳሳቱም እንዲመለሱ ነው።

በመንፈሳዊ ልምምዶች ላይ የሚሰነዘሩ አሳቦች ነባራዊውን እውነታ ማለትም ቅዱስ ቃሉን ሳይመረኮዙ የተሰጡ እንደሆነ አሳባዊ ወይም ግለሰባዊ እና ኅሊናዊ (subjective) ብቻ መሆናቸው አይቀርም። ስለዚህ አንድ ሰው አንድ ነገር ሌላው ሌላ ቢል ሁለቱም የየራሳቸውን ልምምድ እያንጸባረቁ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የሰው አስተያየት እንደሚዛን ከተወሰደ በሁለቱም ልምምዶች ውስጥ የጠለቁትና ሁለቱንም የመረመሩት የተመዛዘነ አስተያየት ሊኖራቸው ይችላል ብዬ አምናለሁ።

በርግጥ ይህ ጽሑፍ ስነ-መለኮታዊ ወይም ትምህርታዊ ወይም ሂሳዊ ወይም ልምምዳዊ ብቻ አይደለም የሁሉም ቅንጫቢ ነው። መንፈስ ቅዱስ እርሱ አምላክ ነው፤ እርሱ የፀጋ ሥጦታ ምንጭ የእውነት አስተማሪ የስብራት ጠጋኝ አምላክ ነው እንጂ የሆነ ነገር አይደለም። እርሱ መለኮታዊ ሰብነት ነው እንጂ መለኮታዊ ኃይል አይደለም። እነዚህን ነገሮች በጽሑፉ ውስጥ ተመልክተናቸዋል። በርግጥ አንዳንዶች ይህን በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይቀበሉታል በተግባር ሚዳ ግን እንደ አምላክነቱ ሳይሆን እንደ ሌላ ነገር ነው የሚያዩት። መንፈስ ቅዱስ እርሱ የእውነት አስተማሪ በመሆኑና ወደ እውነትም ሁሉ የሚመራ አምላክ እንደመሆኑ መጠን በዚህም ውስጥ ያሉትን ነገሮች ከመጽሐፉ

የበለጠና ባሻገርም ሊያስረዳ የታመነ በመሆኑ ደስ ይለኛል።

ስጋዊ ወይም አካላዊ ዕድገት ውስብስብና እየተሳሳቱ የሚማሩበት ሂደት እንደመሆኑ መጠን መንፈሳዊውም ዕድገት እንዲሁ ነው። ብዙ የዕድገት ፈሮችና አቅጣጫዎች ያሉትም ነው። በክርስትና አንፃር መንፈሳዊ ዕድገት ከማናቸውም ከሌሎች በዚህች ዓለም ካሉ ሁሉ ዕድገቶች የበለጠው ነው። ምክንያቱም ይህ ዕድገት ማለት ክርስቶስን ለመምሰል መሰራት ማለት ነው። በበላጭነቱ ልክ ደግሞ ቀላል ያለመሆኑም ግልጽ መሆን አለበት። ማናቸውም ዓይነት ሰዎች ክርስቶስን እንዲመስሉ የሚያደርግ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ዕንቅፋቶችና አደጋዎች ከውጪም ሆነ ከውስጥ ቢኖሩበት ማስደንገጥ የለበትም። በአካላዊ ዕድገት ውስጥ በተለይም ስሜታዊና አዕምሯዊ በሆኑት ዕድገቶች ሲታደግ እያጠፉና ከጥፋትም እየተማሩ ነው። ይህ ጥፋት ሌላ ጊዜ የማይደገም ጥፋት ነው። ይሁን እንጂ ደጋግመው እያጠፉ ደጋግመው የሚቆስሉና የሚጎሳቆሉ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶች እነርሱ ሳያጠፉ ሌሎች ካጠፉትና ከደረሰባቸው በመማር ከውድቀት የሚተርፉ ደግሞ አሉ። መንፈሳዊ ዕድገትና መንፈሳዊ ንቅናቄ በዚህ ይመሳሰላሉ። ማናቸውም ንቅናቄዎች በእንቅስቃሴያቸው ወቅት በሚያልፉበት ጎዳና የሚሳሳቷቸው ነገሮችም አሉ።

መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን ያደለበት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ጎልቶ እንዲታይና ቤተ ክርስቲያንም እንድትታነጽበት መሆኑ ዕውቅ ጉዳይ ነው። መቼም ሆነ የትም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃልና ባህርይ የማይመስልና የሚቃረን ስራ እንደሰራና እንደሚሰራ አናነብብም። ‘ሌላው አጽናኝ’ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ሌላ ዓይነት "ሌላ" ሳይሆን ተመሳሳይ ሌላ ነው። ይህም ማለት የኢየሱስን ባህርይ የሚመስል ያለውና ጌታ በአካለ-ስጋ ከኛ ጋር ቢሆን የሚያደርገውን ስራ የሚሰራ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነውና እርሱ የሚሰራው ስራ የአምላክን ባህርይ የሚፃረር አይደለም።

እንዳለፉት ዘመናት ሁሉ በኛም ዘመን የጌታ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ቀደም ባለው ታሪክ ሁሉ ውስጥ እንደታየው ወደ ሁለቱም ጫፎች ልትጎተትና ልትወጠር ትችላለች። ሚዛኗን ካልጠበቀች አደገኛ ሊደሆን አፍራሽ ማጥ ውስጥ ልትገባ ትችላለች። አንዱ አክራሪ ጫፍ እንደ ብረት የቀዘቀዘ ከሰው-ሰራሽ ብቻ ስርዓት የተነሳ ሕይወት የማይሸት ለሰዎች ስሜት ምንም ቦታ የሌለው የተቀመሩ ደንቦችንና የእምነት አቋሞችን እንደ ግውዝ አማልክት በማድረግ እነርሱ ካሉት ምንም እልፍ ዝንፍ የማይባልበት ለሚደረጉ ለሚባሉና ለሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ሰው-ሰራሽ ገደቦች የተበጁለት ከዚያም አንድ እንኳ ለውጥ የማይደረግበት ወንጌልንም እንደየሰው ባህል፥ ዕድሜ፥ እውቀት፥

ስሜት፥ ሌሎችም ሁኔታዎች ለማዳረስ የሚደረጉ ለውጦችን የሚቃረንና የማይፈቅድ ነው ሌሎችም ይህን መሳይ ነገሮች አሉት። በሌላው አክራሪ ጫፍ ደግሞ ምንም ዓይነት ደንብ የሰውም ይሁን የእግዚአብሔር ሊገዛው በማይፈልግ ልምምዳዊ ፈረስ መጋለብ ነገሮችን በአዕምሮ ማመዛዘንን ኢ-መንፈሳዊ ማሰኘት መንፈሳዊውን ነገር አካላዊ በሆነው ብቻ መለካትና በዚያም መደምደም በየጊዜው እንደ ፋሽን በሚለዋወጡ ስሜታዊ ክንፎች መክነፍ ያም አላረካ ሲል ሌላ አዳዲስ ነገር በመፍጠር ዘለቄታ የሌለው እርካታን መፈለግ በቃሉ ስር ለመስደድ በሥነ-ሥርዓት መማርን ማጥላላትና ልምምዶችን ብቻ እያፈነፈኑ መፈለግ እንዲሁም የመሳሰሉት ይገኙበታል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ጤንነት ንጽሕናና ጥንካሬ ለመጠበቅ ይህን ሚዛን በጌታ ቃል መሠረትና በንጹሕ ኅሊናና በማስተዋልም ሊጠብቁት ይገባል። እግዚአብሔር ልጆቹ ሁሉ የሚያልፈውን በማያልፈው ሳይለውጡ ሊኖሩለት የሚፈልገውን የእርሱን ማንነት የሚያሳይ የልጁንም መልክ የሚያንጸባርቅ ሕይወትን ይኖሩ ዘንድ መሪዎች መጣር አለባቸው። ደግሞም አንድ ሕያው አካል የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊም ሆነ ውጪያዊ አንድነት የሚያናጉ አዝማሚያዎችን በመንፈሳዊው ጦር ዕቃ መፋለምና መልካሙን ገድል መጋደል ይጠበቅባቸዋል።

እውነተኛ መንፈሳዊነት እግዚአብሔር ከልጆቹ ሁሉ የሚጠብቀው ነገር ሲሆን ይህም እውነተኛ መንፈሳዊነት ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ነው። ይህን በማስብና መቅደም ያለበትን በማስቀደም የሌለበትንም በመቅደም እርሱን የሚያስከብር ምዕመናንንም የሚያንጽ ሕይወትና አገልግሎት ይኖረን ዘንድ ጌታ ጸጋውን በጸጋ ላይ አብዝቶ ይስጠን። አሜን።

# የግርጌ ማስታወሻዎች

## ምዕራፍ አንድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማንነት

1 Evangelical Dictionary of Theology፥ ገ.524.

2 በJeremiah Films የተዘጋጀ "Jehovah's Wittnesses" የተሰኘ ዶክሜንተሪ ፊልም።

3 Willmington's Guide to the Bible, pp.653-4.

4 Baptism and Fullness, pp.43-4.

5 The Charismatics, p.123.

6 Encyclopedia of Early Christianity, p.622.

7 Word Study in the Greek New Testament, Vol.I, p.128.

8 The Holy Spirit, p.147.

## ምዕራፍ ሁለት፥ የጸጋ ስጦታዎች

1 Charisma, p.9

2 ማስተር ላይፍ፥ "የጸጋ ስጦታ"፥ ገጽ 4።

3 Spiritual Gifts in the Local Church, p.80.

4 Unwrap Your Spiritual Gifts, p.75.

## ምዕራፍ ሦስት፥ ካሪዝማዊ መነቃቃቶችና እንቅስቃሴዎች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ

1 The Apostolic Fathers, pp.263-5.

2 Ibid., p.71

3 Ibid., pp.196-7

4 Chrismatic Gifts in the Early Church, p.32.

5 Ibid., p.34.

6 Documents of the Christian Church, p.77.

7 Christianity Through Centuries, p.102.

8 Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements, p.470.

9 Ibid., p.850.

## ምዕራፍ አራት፥ ካሪዝማዊ ቀውሶች

1 Fire in the Fireplace, pp.173-5.

2 A Different Gospel, p.xiii.

3 The Pentecostal Movements in the Catholic Church, pp.225-6.

4 The Charismatic Movement, p.37.

5 A Diffrent Gospel, p.66.

6 Ibid., p.67.

7 Charismatic or Christian?, p.147.

8 "መንፈስ ቅዱስ" የቪዲዮ ስብከት።

9 Christianity in Crisis, p.364.

10 Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movement, pp.901-2.

11 Charismatic Chaos, pp.49-50.

12 Ibid., p.161.

13 The Seduction of Christianity, p.33.

14 A Diffrent Gospel, p.110.

15 ገጽ 39።

16 The Serpent Handling Believers, p.57.

17 Ibid., p.161.

18 Ibid., p.101.

19 The Fourth Dimension, pp.36-7.

20 Beyond Seduction, pp.54-5.

21 Christianity in Crisis, pp.74-75.

22 Ibid., p.85.

23 Beyond Seduction, pp.55-6.

24 Ibid., p.56.

25 Christianity in Crisis, pp.70-1.

26 The Seduction of Christianity, p.26.

27 17 Reasons Why I Left the Tongues Movement, pp.14-5.

28 Ibid., pp.73-4.

29 Power Healing, pp.215-23.

30 The Modern Tongues Movements, pp.19-22.

31 The Charismatics, pp.175-8.

32 How to Be Pentecostal Without Speaking in Thoungs, p.11.

33 A Different Gospel, p.151.

34 The Charismatic Movement, pp.231-2.

35 Ibid., 255.

36 Fire in the Fireplace, pp.219-20.

37 The Third Wave of the Holy Spirit, pp.19, 54.

38 Charismatic Chaos, p.130.

39 Power Evangelism, pp.40-1.

40 Charismatic Chaos, pp.141-2.

41 A Different Gospel, pp.171-2.

42 Ibid., pp.173-4.

43 Christianity in Crisis, p.351.

44 Documents of the Christian Church, pp.185-90.

45 A Daily Guide to Miracles, p.63.

46 Christian Research Journal, p.44.

47 Faith Today, p.21.

48 Ibid.,p.27.

49 Ibid., p.25.

# ዋቢ መጻሕፍት


Bettenson, Henry, ed. Documents of the Christian Church, Oxford University Press, N.Y., 1963.

Burgess, Stanley, M.McGee,Gary B.editors with Alexander, Patrick H.associate ed. Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements, Regency Publishers, Grand Rapids, MI.,1988.

Burton, Thomas. The Serpent Handling Believers, The University of Tennessee Press, Knoxville, 1993.

Cairns, Earle E.Christianity through Centuries, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI., 1954.

Campolo, Tony. How to Be Pentecostal without Speaking in Tongues, Word Publishing, Dallas, TX., 1991.

ዳንኤል መኮንን፥ <u>መንፈስ ቅዱስ</u>፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ፥ 1971 እ.ኢ.ት.አቆ።

Elwell, Walter A. ed. Evangelical Dictionary of Theology, Baker Book House, Grand Rapids, MI., 1984.

Ferguson, Everett. [et al] ed., Encyclopedia of Early Christianity Garland Publishing, New York, N.Y., 1990.

Gangel, Kenneth O. Unwrap Your Spiritual Gifts, Victor Books Wheaton, Ill., 1983.

Graham, Billy. The Holy Spirit, Word Books, Waco, Texas, 1978.

Gromacki, Robert Glenn. The Modern Tongues Movement, Presbyterian and Reformed Publishing Co., Philadelphia, 1967.

Grossman, Siegfried. Charisma, Key Publishers Inc., Wheaton, Ill., 1971

Hanegraaff, Hank. Christianity in Crisis, Harvest House Publishers Eugene, Oregon, 1993.

Hamilton, Michael P. ed. The Charismatic Movement, William B. Eerdmans Publishing Co., Grand Rapids, MI., 1975.

Hummel, Charles E. Fire in the Fireplace, IVP, Downers Grove, Ill.,1978.

Hunt, David and McMahon, T.A. The Seduction of Christianity, Harvest House Publishers, Evgene, OR.,1985.

Kydd, Ronald A.N. Charismatic Gifts in the Early Church, Hendrckson Publishers, Peabody, MA., 1984.

McConnell, D.R. A Different Gospel, Hendrickson Publishers, Peabody, Massachussetts, 1988.

MacArthur, John F. The Charismatics, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI.,1978.

MacArthur,John F. Charismatic Chaos, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI., 1992.

O'Connor, Edward D. The Pentecostal Movement in the Catholic Church, Ave Maria Press, Notre Dame, Ind., 1971.

Pohl, Alfred H. 17 Reasons Why I Left the Tongues Movement, Pioneer Baptist Press, Rapid City, SD., 1982.

Pytches, David. Spiritual Gifts in the Local Church, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN.,1985.

Rice, John R. The Charismatic Movement, Sword of the Lord Publishers, Murfreesboro, Tennessee, 1976.

Roberts, Oral. A Daily Guide to Miracles and Successful Living through Seed Faith, Fleming H. Revell, Old Tappan, N. J., 1975.

Roberts, Oral, A Daily Guide to Miracles, Pinoak Publications, Tulsa, OK., 1975.

ሳውዘርን ባፕቲስት ኮንቬንሽን የሰንበት ትምህርት ቦርድ፥ ማስተር ላይፍ ትርጉም፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ፥ 1974 እ.ኤ.አ.።

ስለሺ ዳንኤል፥ መንፈስ ቅዱስ፥ በቶሮንቶ ቤተልሔም የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ ቪዲዮ፥ ቶሮንቶ፥ ካናዳ፥ ኤፕሪል 1993።

Wagner, C. Peter. The Third Wave of the Holy Spirit, Vine, Ann Arbor, CA., 1988.

Wimber, John. Power Evangelism, Harper and Row, San Francisco, CA.,1986.

Wimber,John, Power Evangelism, Harper and Row, San Francisco, CA.,1987.

Wuest, Kenneth S. Word Study in the Greek New Testament, vol.I, Eerdmans, Grand Rapids, MI., 1973.

## መጽሔቶች

Faith Today: "After the Laughter ", March-April 1995, vol.13, 2.

Christian Research Journal: "An Evening with Rodney Howard-Browne", Winter 1995 vol.17, 3.

